ኢፕድ አዲስ ዘመን

ማክሰኞ | 84ኛ ዓመት ቁጥር 112 ታኅሣሥ 22 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 34.50 | ብዕራችን ስኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

ከተረጂነት የተላቀቀ ልማታዊ ማህበረሰብ ለመፍጠር

ገጽ 4

በሁለትዮሽና ቀጣናዊ ጉዳዮች ፍሬያማ ውይይት ማድረጋቸውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አስታወቁ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ ፦ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጌዲዮን ጢሞቲዎስ (ዶ/ር) ከጅቡቲ ፕሬዚዳንት ኢስማኤል ኦማር ጌሌ እና ሌሎች የሀገሪቱ የሥራ ኃላፊዎች ጋር በወደብ አጠቃቀም እንዲሁም በሌሎች የሁለትዮሽና ቀጣናዊ ጉዳዮች ዙሪያ ፍሬያማ ውይይት ማድረጋቸውን አስታወቁ።

በጅቡቲ የሥራ ጉብኝት እያደረጉ ያሉት ሚኒስትሩ፤ ከጅቡቲ ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ጋር ባደረጉት ቆይታ እንዳስታወቁት፤ የጉብኝቱ ዓላማ በሁለትዮሽ እና ቀጣናዊ ጉዳዮች ዙሪያ ምክክር ማድረግ ነው።

በሁለትዮሽና ቀጣናዊ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ኢትዮጵያ ከነፋስ ኃይል 1 ነጥብ 35 ሚሊዮን ሜጋ ዋት ኤሌክትሪክ ማመንጨት የሚያስችል አቅም አላት

- ባለሀብቶች ዘርፉን እንዲያስሙ ምቹ ሁኔታ መፈጠሩም ተጠቆመ

ኢያሱ መሰለ

አቶ ፍሰሃ ጌታቸው

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ከነፋስ ኃይል 1 ነጥብ 35 ሚሊዮን ሜጋ ዋት ኤሌክትሪክ ማመንጨት የሚያስችል አቅም እንዳላት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አስታወቀ። ዘርፉን ባለሀብቶች እንዲያለሙ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፈጠሩን ገለጸ።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙዩኒኬሽን ሥራ አስኪያጅ አቶ ፍሰሃ ጌታቸው በተለይ ለአዲስ ዘመን እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ከነፋስ ኃይል ብቻ 1 ነጥብ 35 ሚሊዮን ሜጋ ዋት ኤሌክትሪክ ማመንጨት የሚያስችል አቅም አላት። በአሁኑ ሰዓት ከዚህ ዘርፍ ማመንጨት የተቻለው ከ400 ሜጋ ዋት የማይበልጥ ነው።

ሀገሪቱ በዘርፉ ካላት ሀብት አንጻር እስከ አሁን የተመረተው ኢምንት እንደሆነ የገለጹት አቶ ፍሰሃ፤ ከንፋስ የሚገኘውን ኃይል ለማሳደግ መንግሥት ከሚሠራው ሥራ በተጨማሪ የግሉ ዘርፍ ቢሰማራ የኃይል አቅርቦት መጠንን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ እንደሚያስችል አመልክተዋል።

የሀገሪቱን የኃይል አቅርቦት መጠን ለማሳደግ በተያዘው አቅጣጫ መሰረት ተቋሙ የንፋስ ኃይል ማመንጫዎችን ሁለተኛ አማራጭ አድርጎ እየገነባ እንደሚገኝ ገልጸው፤ የንፋስ ኃይል ማመንጫዎች ለብሄራዊ የኃይል ቋቱ የሚኖራቸውን አስተዋጽኦ ለማሳደግም ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

የነፋስ ኃይል ማመንጫ ግንባታዎች ከ14 ዓመት ወዲህ መገንባት እንደጀመሩ የተናገሩት አቶ ፍሰሃ፤ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉት ጥቂት የንፋስ ኃይል ማመንጫዎች ናቸው ብለዋል።

ኢትዮጵያ ከነፋስ ኃይል... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

በችግሮች እየተፈተነ ያለው የቆዳና ቆዳ ውጤቶች የውጪ ንግድ

ጽጌረዳ ጫንያለው

ዜና ትንታኔ

ኢትዮጵያ በእንስሳት ሀብቷ ቀዳሚና የተሻለ አቅም ያላት ሀገር ብትሆንም በቆዳና ቆዳ ውጤቶች የምታገኘው የውጭ ገቢ ግን ከዓመት ዓመት እያሽቆለቆለ እንደመጣ ይገለጻል። ተግዳሮቶቹም በርከት ያሉ እንደሆኑ ይነገራል። ይህ ለምን ሆነ፤ ተግዳሮቶቹ ምን ምን ናቸው፤ የመፍትሄ አማራጮቹስ? የተለያዩ በዘርፉ የሚሰሩ አካላት ሀሳባቸውን አጋርተውናል ።

አቶ ዙልፊከር አባጅሃድ ይባላሉ። በቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት ማዕከል ሥራ አስኪያጅ ናቸው። ኢትዮጵያ ከፍተኛ የእንስሳት ሀብት ካላቸው ሀገራት ተርታ ብትመደብም ከአላት ሀብት አኳያ ግን ከቆዳ ኢንዱስትሪው ዘርፍ በሚፈለገው ልክ ተጠቃሚ እንዳልሆነች ይናገራሉ። በተለይም

በችግሮች እየተፈተነ... ወደ ገጽ 3 ዞሯል

በዓልን ተከትሎ የአቅርቦት እና የፍላጎት አለመጣጣም እንዳይኖር እየተሠራ ነው

ሔርሞን ፍቃዱ

አዲስ አበባ፡- በሸገር ከተማ አስተዳዳር ከበዓል ጋር ተያይዞ የሚያጋጥም የአቅርቦትና የፍላጎት አለመጣጣም እንዳይኖር አስቀድሞ እየተሠራ መሆኑን የሸገር ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ገለጸ።

የሸገር ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት መጋቢ ስርዓት ቀሲስ ታዬ ለታ ለአዲስ ዘመን እንደገለጹት፤ በዓላት በመጡ ቁጥር የሚያሳስበው የአቅርቦት እና የፍላጎት አለመመጣጠንን ተከትሎ የሚከሰት የዋጋ ጭማሪ ነው።

አሁን ላይ ችግሩን ለመፍታት ከነጋዴው እና ከንግድ ቢሮ ጋር በተቀናጀ እየተሰረ እንደሆነ ያመለከቱት ፕሬዚደንቱ፤ ነጋዴዎች በተለይ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ቀድሞ በማስገባት ገበያው እንዲረጋጋ የማድረግ ሚናቸውን እንዲወጡ ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል።

ሀገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች የአቅርቦት እጥረት እንዳያጋጥምና አላስፈላጊ ጭማሪ እንዳይደረግባቸው ነጋዴዎች በተለያዩ መድረኮች ስልጠና እያገኙ እንደሆነ ጠቅሰው፤ የሚሰጡት አገልግሎት ለራሳቸው ማህበረሰብና ለዜጋቸው መሆኑን ተረድተው ምርቶችን በተገቢው መንገድ ለማቅረብ እየሰሩ እንደሚገኙ አመልክተዋል።

የኦሮሚያ የንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከበዓሉ ጋር ተያይዞ የመግዛት ዓቅማቸው ዝቅተኛ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ባዛሮችን ማዘጋጀቱን ጠቅሰው፤ አብዛኞቹ የሀገር ውስጥ ምርቶች ፤ እንደ ዘይት እና ሱኳር ያሉ መሰረታዊ ሸቀጦች እጥረት እንዳያጋጥም ምክር ቤቱ ላለፉት ዓመታት ሲሰራ እንደቆየም ገልጸዋል።

ንግድ ምክር ቤቱ ትልቅ ዓላማ ያነገበ መሆኑን የጠቀሱት ፕሬዚዳንቱ፤ ከሀገር ውጭ በአሜሪካ እና በጀርመን ኤክስፖዎቹን ማካሄዱን አመልክተዋል፤ ከበአላት ጋር ተያይዞ ሸማቹ ማህበረሰብ ሸቀጦች በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲገበያይ ስርዓት በመዘርጋት አመርቂ ውጤቶች እያስመዘገበ ይገኛል ብለዋል።

ውጭ ሀገር የሚገኙ የዲያስፖራ አባላት ሀገር ውስጥ ገብተው በተለያዩ የስራ ዘርፎች እንዲሳተፉ እያደረገ መሆኑንም፤ አፖሎ የተባለ ትልቅ ካምፓኒ ዘመናዊ የሪልስቴት ለመገንባት ከምክር ቤቱ ጋር ሰፊ ውይይት ማደርጉንና ጥናቱን አጠናቆ ለማስረከብ በዝግጅት ላይ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

የወተት ምርትን ለሸገር እና ለአዲስ አበባ ከተማ ለማቅረብ በከብት እርባታ እና በወተት ተዋፅኦ ምርት መሰማራት የሚፈልጉ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ባለሀብቶች እንደቀረቡም ገልጸዋል።

ማህበረሰቡ የማይጠቀምበት ንግድ ጤናማ አይሆንም ያሉት ፕሬዘዳንቱ ፤ ህገወጥ ንግድ እና በአቋራጭ ለመክበር የሚደረግ እንቅስቃሴ ጎጂ መሆኑን በመረዳት ነጋዴው ምርቶችን አስቀድሞ በማቅረብ ህብረተሰቡ በዓሉን በደስታ እንዲያከብር በጋራ እንዲሠሩ ጥሪ አቅርበዋል።

አዋጁ ኢትዮጵያን በዓለም አደባባይ ከፍ የሚያደርግና ተቀባይነቷን የሚጨምር ነው

ታምሬት ተስፋዬ

አቶ ከበደ ይማም

አዲስአበባ፡- የአረንጓዴ አሻራና የተጎሳቆለ መሬት ማገገሚያ ልዩ ፈንድ ማቋቋሚያና አስተዳደር አዋጅ መውጣት ኢትዮጵያን በዓለም አደባባይ ከፍ የሚያደርግና ተቀባይነቷ እንዲጨምር የሚያደርግ መሆኑን የኢትዮጵያ ደን ልማት አስታወቀ።

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 12ኛ መደበኛ ስብሰባው የአረንጓዴ አሻራና የተጎሳቆለ መሬት ማገገሚያ ልዩ ፈንድ ማቋቋሚያና አስተዳደር አዋጅን መርምሮ በሙሉ ድምጽ ማፅደቁ የሚታወስ ነው።

ይህን አስመልክቶ የኢትዮጵያ ደን ልማት ዋና ዳይሬክተር አቶ ከበደ ይማም ለአዲስ ዘመን እንደገለጹት፣ የአየን ንብረት ለውጥ፣ ብክለትና ብክነት የምድራችን ዋነኛ ፈተና መሆን ከጀመረ ዋል አደር ብሏል። ለዚህ የዓለም ዋነኛ ስጋት ተጨባጭና ተግባራዊ ምላሽ በመስጠት ኢትዮጵያ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናት። ከ2010 ጀምሮ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ሃሳብ አመንጪነትና በመላ ሕዝቡ ተሳትፎ ተግባራዊ በመደረግ ላይ የሚገኘው የአረንጓዴ አሻራ ለዚህ ማሳያ ነው።

ይህን ጥረት ይበልጥ በሚደግፍ መልኩ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአረንጓዴ አሻራና የተጎሳቆለ መሬት ማገገሚያ ልዩ ፈንድ ማቋቋሚያና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1361/17 ማፅደቁን ያስታወሱት አቶ ከበደ፤ የአዋጁ መውጣትም የኢትዮጵያ መንግሥት ለተፈጥሮ ሀብትና አካባቢ እንክብካቤ እንዲሁም የአካባቢ ብክለትና ብክነትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ያለውን ሁለንተናዊ ቁርጠኝነት በግልፅ ያሳያል»ብለዋል።

ትግበራው ከመንግሥት በጀት እንዲመደብ የሚያስችል መሆኑንና ደኖችን ለመንከባከብና ለማልማት አረንጓዴ አሻራን ለማስፋፋት አቅም የሚፈጥር መሆኑን ያስገነዘቡት አቶ ከበደ፤ «ለዘርፉ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት የሀገር መሪ የእለት እለት አጀንዳ ሲሆንና ለውጤታማ ትግበራውም ሀብት ተመድቦለት ወደ እንቅስቃሴ ሲገባም በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው ነው»ብለዋል።

የአዋጁ መውጣት ኢትዮጵያን በዓለም አደባባይ ከፍ የሚያደርግና ተቀባይነቷን ከፍ የሚያደርግ መሆኑንም አስገንዝበዋል። ኢትዮጵያ በደን ዘርፍ ከልማት አጋሮችና ከሌሎች ዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ፋይናንስ ሰጪ ምንጮች እና ከካርበን ግብይት ሥርዓቶች የምታገኘውን ድጋፍና ጥቅም ለማሳደግ የሚያስችል መሆኑንም ጠቁመዋል።

በሰሜን ሸዋ ዞን ጾታዊ ጥቃትና ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶችን በሚፈጽሙ ላይ ተጽዕኖ የመፍጠር እንቅስቃሴ ተጀመረ

መልካምሥራ አፈወርቅ

ዜና ሐተታ

በሰሜን ሸዋ ዞን በህብረተሰቡ ውስጥ ሆነው ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶችና ጾታዊ ጥቃቶችን በሚፈጽሙ ግለሰቦች ላይ ተፅዕኖ የመፍጠር እንቅስቃሴ መጀመሩ ተገለጸ።እንቅስቃሴው ድርጊቱን የፈጸሙ ግለሰቦችን ከዕድር፣ ከማህበርና መሰል እንቅስቃሴዎች ማግለልና ሙሉ በሙሉ ማስወጣትን ተሳቢ ያደረገ ነው።

በዞኑ ሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ ወይዘሮ የሮምነሽ ጋሻውጠና ለአዲስ ዘመን እንደገለጹት፤ ጾታዊ ጥቃትን ጨምሮ የተለያዩ ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶችን በሚፈጽሙ ግለሰቦች ላይ ሕብረተሰቡ ተጽዕኖ የመፍጠር ሥራን ዕውን ማድረግ ጀምሯል።

በዞኑ ከተወሰኑ ጊዜያት ወዲህ ከሚስተዋለው የሰላም ዕጦት ጋር ተያይዞ ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶች ተበራክተዋል ያሉት ኃላፊዋ፤ በአሁኑ ጊዜም በተለይ በሴቶችና ህጻናት ላይ የሚደርሰው ጾታዊ ጥቃት እየተባበሰ መሄዱን ተናግረዋል።

እንደኃላፊዋ ገለጻ፤ በዞኑ በ2016 ዓም በቁጥር 64 የሚሆኑ ጾታዊ ጥቃቶች ተፈጽመዋል። ከነዚህ መሀልም 23ቱ ከስድስት ዓመት ጀምሮ ባሉ ህጻናት ላይ የተፈጸሙ ጥቃቶች ናቸው።ይህ አሀዝ ለፖሊስ ሪፖርት የተደረገውን ብቻ የሚያመለክት ነው ያሉት ኃላፊዋ፤ ድርጊቱ ከዕለት ወደዕለት እየጨመረ መሄዱ የሁኔታውን አሳሳቢነት ከፍ አድርጎታል ብለዋል።

ወይዘሮ የሮምነሽ እንደሚሉት፤ በአሁኑ ጊዜ ወንጀሉን ፈጽመዋል የተባሉ 31 ግለሰቦች በህግ ቁጥጥር ሥር ውለዋል። ተጠርጣሪዎቹን በፍርድ ሂደት ውሳኔ ለማሰጠትም እንቅስቃሴው ተጠናክሮ ቀጥሏል።

በዞኑ የተለያዩ ቦታዎች ያለ ዕድሜ ጋብቻን ጨምሮ ሌሎች ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶች ይፈጸማሉ ያሉት ኃላፊዋ፤ ዘንድሮ ግን በተለይ በሴቶችና ህፃናት ላይ ጾታዊ ጥቃት ይብቃ ያሉ የተለያዩ ወረዳ ነዋሪዎች የራሳቸውን ህግና መመሪያ አውጥተው ተፅዕኖ የመፍጠር ውሳኔ መጀመራቸውን ገልጸዋል።

እንደ ኃላፊዋ ማብራሪያ ተጽዕኖ የመፍጠር ተግባሩ ያነጣጠረው ድርጊቱን የፈጸሙ ግለሰቦችን ከዕድር፣ ከማህበርና መሰል እንቅስቃሴዎች በማግለልና ሙሉ በሙሉ በማስወጣት ነው። ይህ ውሳኔም ሞት ባጋጠመ ጊዜ ቀብር እንዳይፈጸምላቸው እስከማድረግ የደረሰ ቁርጠኝነት አለው።

በሰሜን ሸዋ ዞን 31 ወረዳዎች ውስጥ 9 የከተማ አስተዳደሮች ይገኛሉ። ይህ በጎ ጅምር ውሳኔው ባልተዳረሰባቸው አካባቢዎች ጭምር ተጠናክሮ እንዲቀጥል እንፈልጋለን ያሉት ኃላፊዋ፤ በተለይ የዕምነት ተቋማትና የዕድር ማህበራት በማህበረሰቡ ዘንድ ተጽዕኗቸው ከፍ ያለ በመሆኑ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል ብለዋል።

በ2017 ዓ.ም የፍትህ አካላት ድርጊቱን ከመከላከል ባሻገር ጾታዊ ጥቃቶች ተፈጽመው ሲገኙ የህግ ተጠያቂነቱን መጠናከር የሚቻልበትን አሰራር ዘርግተዋል። ኃላፊዋ እንደሚሉትም፤ አሰራሩ ከክልል ጀምሮ የተዋቀረ በመሆኑ የሚመለከታቸው አካላት ጭምር የምክክር ሰነድ ተፈራርመው የጋራ ውሳኔ አሳልፈዋል። ጥቃቱ የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ ምክንያት ያደረገ ከመሆኑ ጋርም በተለየ ትኩረት እየተሰራበት እንደሆነም አክለው ገልጸዋል ።

በዞኑ በጾታዊ ጥቃት ሳቢያ ሥነልቦናቸው የተጎዳና ኤኮኖሚያቸው የሚደገፍ ወገኖች መኖራቸውን የጠቀሱትት ወይዘሮ የሮምነሽ፤ ውጤታማ ተግባር ላይ ለመድረስም ግንዛቤ ከማስጨበጥ ባለፈ የሚመለከታቸውና በጎ አድራጊ ተቋማት በበቂ በጀትና አቅም የታገዘ ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል ሲሉ አስታውቀዋል።

ችግሮችን በመፍታት ዘርፉ ዋንኛ የውጪ ምንዛሬ ምንጭ ሊሆን እንደሚችል ተጠቆመ

መክሲት ወንድወሰን

አዲስ አበባ፡- በጥራጥሬና ቅባት እህሎች የውጪ ንግድ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በአግባቡ መግታት ከተቻለ ዘርፉ ዋነኛ የውጪ ምንዛሬ ምንጭ ሊሆን እንደሚችል አንድ ጥናታዊ ጽሁፍ አመለከተ። ኢትዮጵያ በቅባት እህሎች እና ጥራጥሬ ምርቶች ያላትን እምቅ አቅም ለመጠቀም ዘርፉን የሚመሩ ተቋማት በጋራ መስራትና መናበብ እንዳለባቸው ተመለከተ ።

የጥራጥሬና ቅባት እህሎች ላኪ ማህበር ከጂ አይ ዜድ ጋር በመተባበር ያስጠናው ጥናት ይፋ ሆኖ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት በተደረገበት ወቅት እንደተገለጸው፤ ዘርፉ ከፖሊሲ ፤ ከህግ እና ከሴክተር መስሪያ ቤቶች አፈጻጸም ጋር የተያያዙ ችግሮች አሉበት።

ጥናቱ እንዳመለከተው፤ ከፖሊሲ ጋር በተያያዘ በርካታ ማሻሻያ የሚፈልጉ ጉዳዮች አሉ፤ የመጀመሪያው እና ለዘርፉ እድገት ማነቆ የሆነው ከመሬት ጋር የተያያዘ፤ ዘርፉን የሚቀላቀሉ ኢንቨስተሮች መሬት የሚያገኙበት ሂደት የሚያስረዝመው ቢሮክራሲያዊ አሰራር ነው።

ሰብሎችን በሰፋፊ የእርሻ መሬት በማምረት በፋብሪካ ፕሮሰስ ለማድረግ የሚፈልጉ አልሚዎች መሬት ለማግኘት በአማካኝ 12 ወራት ይወስድባቸዋል። ይህ ደግሞ ባለሀብቶች ወደዘርፉ በስፋት እንዳይገቡ ማነቆ ሆኗል።

ከቅባት እህል እና ጥራጥሬ ግዥ ጋር ተያይዞ ያለው አሰራር በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በኩል ብቻ እንዲያልፍ የተደረገበት ሁኔታ በራሱ ተጨማሪ ችግር መሆኑ በጥናቱ ተጠቁሞ ፤ይህም ተጨማሪ የግዥ መንገዶች እንዳይኖሩ ተግዳሮት መሆኑን አስታውቃል። አሁን ላይ የቀጥታ ግዥ ሂደት እና የውል እርሻ አሰራሮች ወደ ስራ ላይ እየገቡ መሆናቸው ችግሩን በተሻለ መንገድ ሊያቃልሉ እንደሚችሉ፤ ይህም ሆኖ አሁንም አተገባበር ላይ ክፍተቶች መኖሩን በጥናቱ ተጠቁሟል።

ሌላኛው የዘርፉ ፈተና ዓለም አቀፍ የገበያ ዋጋ አለመረጋጋት መሆኑን፤ በተለያዩ የአለም ሃገራት የሚደረጉ ጦርነቶች እና የኑዳጅ ዋጋ መጨመር የአለም አቀፍ ገበያው የተረጋጋ እንዳይሆን ማድረጉ። ይህም የአርሶ አደሩን እና የላኪዎችን የዋጋ ግመት በማዛባት ተጠቃሚነታቸውን ችግር ውስጥ መክተቱን አስታውቋል።ችግሩን ለመፍታት መንግስት የወደፊት ውል (ፊውቸር ኮንትራት) እና የሰብል ኢንሹራንሶች በፖሊሲዎች እንዲደገፉ ማድረግ አለበት። ይሄውም የዋጋ ግመታ መዛባት ቢጋጥምም በተወሰነ መልኩ አርሶ አደሩ እና ላኪውን ከኪሳራ ሊጠብቀው እንደሚችል ጥናቱ አመልክቷል።

እንደ ጥናቱ ውጤት ፤ኤዥያን ሀገራት ከአውሮፓውያኑ ጋር ሲነጻጸር ለጥራት ያላቸው ግምት ዝቅተኛ እና ተለዋዋጭ መሆኑ አብዛኛውን የኢትዮጵያ የወጭ ንግድ የሚፈጸመው ከእነሱ ጋር እንዲሆን አድርጓል። ይህም ሆኖ ሀገራቱ አስተማማኝ የንግድ ማዕከል መሆን አለመቻላቸው እና የሚከፍሉት ክፍያ ዝቅተኛ መሆኑ ኢትዮጵያ ለምታመርተው ምርት ተገቢውን ክፍያ እንዳታገኝ አድርጓል።

እንደ አውሮፓውያን ህብረት ያሉ ሀገራት ለምርት ጥራት ከፍተኛ ትኩረት ቢሰጡም የሚከፍሉት ክፍያ እና የሚወስዱት ብዛት አስተማማኝ ነው። በመንግሥት በኩል ለዚህ የሚያፈልጉ የሰርተፍኬት አሰጣጥ ሂደቶች እና የላብራቶሪ ማረጋገጫዎችን የማዘጋጀት ስራዎችን ሊሰራ ይገባል ።

የድፍድፍ ዘይት እና ተመርቶ የተጠናቀቀ ዘይትን ለሚያስገቡ ባለሃብቶች የሚደረገው የድጎማ አሰራር ሸማቹን ማህበረሰብ የሚጠቅም ቢሆንም ሀገር ውስጥ ያሉ አምራቾችን የሚጎዳ እንደሆነ አመልክቷል።

ሁኔታዎችን በማቻቻል እና የሀገር ውስጥ አምራቾችን በመደገፍ ለድፍድፍ ዘይት የሚወጣውን የውጭ ምንዛሬ ማዳን ይገባል። እሴት የተጨመረባቸውን ምርቶችም ለውጭ ኤክስፖርት እንዲደረጉ በማድረግ የውጭ ምንዛሬን ለማግኘት ሊሰራ ይገባል።

በየክልሉ ያሉ የሰርቪስ አሰጣጥ ሂደቶች እና የሰሊጥ ምርት ወደ ቻይና ሲላክ ክፍያው የሚፈጸመው በንግድ ባንክ ብቻ መሆኑ ኤክስፖርተሮቹን እየፈተነ የሚገኝ ጉዳይ መሆኑም በጥናቱ እንደ ማነቆ የተነሳ ነው።

በውይይቱም ተሳታፊ የሆኑ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ ላኪዎች በበኩላቸው፤ የአኩሪ አተር ምርት በውጭ ገበያው ላይ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያለው ቢሆንም በሀገር ውስጥ በቂ ምርት መመረት አለመቻሉ እና ገበሬዎች የሚከተሉት የአስተራረስ ዘዴ ኋላ ቀር መሆኑ ለላኪዎች ፈተና ነው።

በመንግሥት በኩል እየተደረገላቸው ያለው የታክስ ማበረታቻ እና የገንዘብ ወለድ መጠን ዝቅተኛ መሆን ጥሩ የሚባል ቢሆንም ባንኮች ለብድር ሲጠየቁ ገንዘብ የለንም ማለታቸው፤ ኤክስፖርተሮች እቅድ የሌላቸው እና አንድን ባለሃብት ስላዋጣው ብቻ እነሱንም የሚያዋጣ ስለሚመስላቸው ወደ ዘርፉ መቀላቀላቸው ለዘርፉ ትልቅ ማነቆ መሆኑን ተናግረዋል። በምርት ገበያ በኩልም የምርት ጥራን ለማስጠበቅ የሚደረገው አሰራር መልካም መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በቅባት እህሎች እና ጥራጥሬ ምርቶች ያላትን እምቅ አቅም ለመጠቀም ዘርፉን የሚመሩ ተቋማት በጋራ መስራትና መናበብ እንዳለባቸው ጠቁመው፤ በቀጣይ ከጥናቱ አጥኚዎች ጋር በጋራ በመስራት ተጨባጭ ለውጥ እንዲመጣ ማድረግ እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል።

በችግሮች እየተፈተነ ያለው የቆዳና ቆዳ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ከውጭ ምንዛሬ ግኝት አንጻር ከዓመት ዓመት እየቀነሰች እንደሄደች ያስረዳሉ።

በኩብት ደረጃ ብቻ ወደ 165 ሚሊዮን የሚደርስ ሀብት ያላት ኢትዮጵያ ሀብቷን እሴት ጨምራ መጠቀም ባለመቻሏ ባለፉት 10 ዓመታት ውስጥ በኤክስፖርት ዘርፉ ከቡና ቀጥሎ ገቢ በማስገኘት የሚጠቀሰውን ዘርፍ አሁን ላይ ወደ 30 ሚሊዮን በማይበልጥ ዶላር ገድባዋለች። የውጭ ገቢዋንም ከአንድ ሦስተኛ እንዳይወጣ አድርጋዋለች ብለዋል። ለዚህም መንስኤው ዘርፈ ብዙ እንደሆነ አስረድተዋል።

እንደ አቶ ዙልፈኪር ገለጻ፤ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች የውጭ ምንዛሬ ግኝት መቀነስ ምክንያት በማዕከል ደረጃ በተሰራው ጥናት ተለይቷል። ሰባት መሰረታዊ ችግሮች እንደሆኑም ታውቋል። አንደኛው በክላስተርና ግብዓቱ በሚገኝበት አቅራቢያ ላይ የተተከሉ ኢንዱስትሪዎች አለመኖራቸው ወይም የአቀማመጥ ሁኔታቸው የተበታተነ ሲሆን፤ ሁለተኛው የስጋ ተረፈ ምርት የሆነው ቆዳና ሌጦ ክትትልና ድጋፍ ስለማይደረግበት ከጥራት አንጻር ችግር እያጋጠመው መሆኑ ነው። በሦስተኛ ደረጃ ላይ የሚጠቀሰው ደግሞ የቴክኖሎጂ አቅም ውስንነት ነው።

ያለቀለት ቆዳን ማምረትና በተለያየ ዲዛይን ለዓለም አቀፍ ገበያው ለሚቀርብ የተሻለ የቴክኖሎጂ እውቀት ያስፈልጋል። በተጨማሪም ማሽኖች ሊኖሩ ይገባል። ይህንን ከማሟላት አንጻርም ኢንዱስትሪዎቻችን በእጅጉ ውስንነት አጋጥሟቸዋል የሚሉት አቶ ዙልፈኪር፤ በአራተኛ ደረጃ የተለየው ተግዳሮት ዓለም አቀፍ ደረጃን አለማሟላት እንደሆነ ጠቅሰዋል። በማህበራዊና አካባቢያዊ ተጽዕኖ ምክንያት ወደ ኋላ መጎተት፤ በዓለም አቀፍ አዲቱ የሚፈለገው ደረጃ ላይ አለመቀመጥ እንደ አንድ ችግር ተደርጎ ተወስዷል ብለዋል።

አንድ የቆዳ ፋብሪካ ሌጦን ያለቀለት ደረጃ ላይ ለማድረስ ቢያንስ ወደ 60 አይነት ኬሚካል ይጠቀማል። ከ95 በመቶ በላይ የሚሆኑት ኬሚካል የሚመጣውም ከውጪ በውጪ ምንዛሬ ነው። በተጨማሪም ፋብሪካዎች ያለቀለት ቆዳና ሌጦን ለማውጣት ቢያንስ 21 ቀን ይፈጅባቸዋል። ለዚህም በቀጣይነት ምርት ለማምረት የሚያስችለውን ጥሬ እቃ ቀድመው ማስገባት ይኖርባቸዋል። ቢያንስ ለስድስት ወር ያህል ሥራቸውን ሊያከናውኑበት የሚችል ግብዓት በስቶክ መያዝ አለባቸውም። ይህንን ለማድረግ ደግሞ የግድ ፋይናንስ ሊኖራቸው ግድ ይላል። በመሆኑም እነዚህን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችላቸው የፋይናንስ አቅም ውስንነት ችግር አንዱና አምስተኛው ተግዳሮት መሆኑንም አንስተዋል።

ስድስተኛው ከገበያ አማራጭና ራስን ማስተዋወቅ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ችግር ነው የሚሉት ሥራአስኪያጁ፤ በአለማቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪና ተመራጭ ለመሆን መጀመሪያ መደረግ ያለበት ራስን መሸጥ ነው። ማንነትን፣ ምን እንዳለ በሚገባ ማሳወቅ ያስፈልጋል። ኤክዚቢሽኖች ላይ መሳተፍ፤ የራስን ብራንድ መስራት፤ ምርትን እያሳዩ የገበያ ትስስር መፍጠር ዓለም ከመጠቀባቸው ተግባራት መካከል ናቸው። እንደ ሀገር ግን ይህ እየሆነ አይደለም። በዚህም አንዱ ተግዳሮት ተደርጎ የተወሰደው የገበያ አማራጭና ራስን ማስተዋወቅ እንደሆነ ተናግረዋል።

ሌላውና ሰባተኛው የተለየው ችግር ተቋማት በትስስር ያለመስራታቸው ሁኔታ ሲሆን፤ የግብይት ስርዓቱን የሚከታተለው አካል፤ የእንስሳት ሀብቱን የሚመለከተው አካል፤ የቴክኒካል ድጋፍ ላይ የሚሰሩ አካላትን ጨምሮ ተናቦ ሲሰራ አይታይም። በዚህም ጥራት ያለው ምርትን አቅርበን ገቢያችንን በሚፈለገው መልኩ እንዳናደርግ ተገድበናል ሲሉ አብራርተዋል።

የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪዎች ማህበር ዋና ጸሀፊ አቶ ዳኛቸው አበበ በበኩላቸው፤ በቆዳና ቆዳ ውጤቶች የሚገኘው ገቢ የቀነሰበት ምክንያት ብዙ ቢሆንም በዋነኛነት የሚጠቀሰው ችግር የጥራት ችግር እንደሆነ ይናገራሉ። 60እና 70 በመቶ በጥራት የሚገኘው ቆዳ 20 በመቶ ላይ እንዲቀመጥ ያደረገው በቆዳና ሌጦ ኮርፖሬሽን እንዲሁም በግብርና ኤክስቴንሽን ደረጃ የሚደረገው ቁጥጥር በመቋረጡ ይህ ሁኔታ እንደተፈጠረም አስረድተዋል።

35 በመቶ በእርድ ወቅት የሚፈጸም ችግር ሲሆን፤ 65 በመቶ የሚሆነው ደግሞ በቁም እንስሳት ላይ የሚፈጠር ችግር እንደሆነ የሚናገሩት አቶ ዳኛቸው፤ ባለፈው ስምንት ዓመታት በከፊል የለፋ ቆዳ እንዳይወጣ በሕግ መታገዱና ወደ ውጪ ገበያው ከተገባ በ150 በመቶ ታክስ ይደረጋል መባሉ አንዱ ለገቢ ቅነሳው አስተዋጽኦ እንደነበረው ተናግረዋል።

መፍትሄው አንድ ነው። ችግሩን ለይቶ ወደ ሥራው መግባት። ለዚህ ደግሞ መንግሥት ቁርጠኛ ሆኖ በጥናት ጭምር የተለየ ሥራ ሰርቷል። በርካታ ለውጦችም እየመጡ ይገኛሉ የሚሉት አቶ ዙልፈኪር፤ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት የሚመራ አንድ የኢንዱስትሪ አምራች ካውንስል እንደተቋቋመና ማን ምን ይሰራል የሚለው ተለይቶ ወደ ስራ እንደትገባ አመላክተዋል። እያንዳንዱ ተቋም የራሱን እቅድ አቅዶ ወደ ሥራ መግባቱንም ገልጸዋል። አምራች ካውንስሉ በሁሉም ዘርፍ ላይ ያሉ አመራሮችን ያካተተ በመሆኑ በዘርፉ በተለይም ከፍተኛ አቅም ባላቸው ኩባንያዎች ያሉ ችግሮችን ለይቶ እየሰራ ስለመሆኑም ጠቁመዋል።

በአገዋ ምክንያት ሥራ አቁመው የነበሩ ኩባንያዎች ሌሎች አማራጮችን ተጠቅመው እንዲሰሩ መደላደሎች እንደተፈጠሩ አንስተውም፤ አሁን ላይ የገበያ አማራጫቸው አሜሪካ ብቻ የሆኑ አምራቾች አፍሪካ ሀገራት እያጥለቀለቁ እንደሆነና ገቢውን በተቻለ መጠን ከፍ እያደረጉ እንዳሉም አስረድተዋል።

አቶ ዳኛቸው በበኩላቸው እንደሚሉት፤ አሁን ላይ እየተሰሩ ባሉ ተግባራት መፍትሄዎቹ እየታዩ ናቸው። ለአብነትም በከፊል የለፋ ብቻ ሳይሆን የአለቀለት ቆዳ ጭምር እንዲላክ መፈቀዱ፤ ያለቀለት ጫማና ቦርሳ እንዲሁም ሌሎች ምርቶችን ለውጪ እንዲቀርብ መደረጉ እንደ ሀገር የተሻለ ገቢን እንድናገኝ አስችሎናል። ይሁን እንጂ ያለው ችግር ቀላል የሚባል ስላልሆነ ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት በትኩረት መስራት ይርባቸዋል። ዘርፉ ማህበረሰቡን ጭምር ያሳተፈ በመሆኑ ግንዛቤ የመፍጠሩ ጉዳይም ትኩረት ሊቸረው ይገባል።

ዘርፉ እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ በዓመት እስከ 130 ሚሊዮን ዶላር ከቆዳና ቆዳ ውጤቶች ምርት ገቢ ያስገኝ ነበር። ከ2010 ዓ.ም በኋላ ግን ይህ ሁኔታ በእጅጉ ቀንሷል። የ2016ዓ.ም ከአጠቃላይ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ገቢም 27 ሚሊዮን ዶላር ብቻ ነበር። 2017 ዓ.ም የአምስት ወሩ የተገኘው ደግሞ 10 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር ነው።

ሁለቱም ባለድርሻ አካላት የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ምርት ሀገሪቱ ከአላት ሀብት አንጻር ቢሰራበት የወጪ ገቢው ብቻ ሳይሆን የሀገር ውስጥ ገቢም በእጅጉ ኢኮኖሚዋን የሚደግፍ እንደሆነ አስረድተዋል። በተጨማሪም ባለፉት ዓመታት ሀገሪቱ ታስገኘው የነበረውን የውጪ ምንዛሬ በእጥፍ ለማሳደግ የሚቻልበት ሁኔታ እንደሚፈጠር ጠቁመዋል። ይህ ካልሆነ ደግሞ ችግሩ ከዚህም እንደሚብስ ተናግረዋል።

ከተረጂነት የተላቀቀ ልማታዊ ማህበረሰብ ለመፍጠር

ማህሌት አብዱል

ዜና ትንታኔ

ከተረጂነትና ከጠባቂነት አስተሳሰብ የተላቀቀ፣ ሀገር የሚያለማ ማህበረሰብ ለመፍጠር የሁሉም ቁርጠኝነት እንደሚያስፈልግ የግብርና ሚኒስቴር ማስታወቁን ጠቅሰን በቅርቡ መዘገባችን ይታወሳል። መንግሥት ተረጂ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ህይወት በዘላቂነት ለመቀየር ያስችል ዘንድ «ከተረጂነት ወደ ምርታማነት» የሚል ንቅናቄ በ11 ክልሎች እየተገበረ ነው። ይህ ንቅናቄ በተጨባጭ መሬት ላይ እንዲወርድና ኢትዮጵያ ላሰበችው የምግብ ሉዓላዊነት የማስከበር ሀገር አቀፍ ጥረት እንዲፋጠን ምን አይነት ሥራዎች ሊከናወኑ ይገባል? ስንል የዘርፉን ባለሙያዎች አናግረናል።

በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የግብርና ኢኮኖሚክስ ዳይሬክተርና ተመራማሪ ዶክተር ታደለ ማሞ እንደሚሉት፤ በኢትዮጵያ የዜጎችን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ለረጅም ጊዜ የተለያዩ መርሃ-ግብሮች ተነድፈው ተግባራዊ ተደርጓል። ይሁንና እነዚህ መርሃ ግብሮች የጠባቂነትና የተረጂነት ስሜት ፈጥሯል ተብሎ በባለሙያዎች ይተቻል። ያንን ተከትሎ ልማታዊ ሴፍትኔት እንዲተገበር የተደረገ ሲሆን፤ ይህም ተረጂዎች እየሰሩ የሚደገፉበትና ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ከእርዳታ ሥርዓቱ የሚወጡበት ሁኔታ በመፍጠር የጠባቂነት መንፈስን ለማስወገድ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል። ይህም ሆኖ ግን ጥቂት የማይባለው ሰው ከመርሃ-ግብሩ ተመርቆ ለመውጣት ያለመፈለግ ዝንባሌ ይታይባቸዋል።

በሌላ በኩልም አስፈፃሚው አካል የግልፀኝነትና ተጠያቂነት ሥርዓት ባለመዘርጋቱ ለመርሃ-ግብሩ የተመደበው በጀት ለምዝበራ የተጋለጠበት ሁኔታ ተፈጥሮ እንደነበርም ያስታውሳሉ። መንግሥት ይህንን በመገንዘብ ከልማታዊ ሴፍትኔት መርሃ-ግብሩ ጎን ለጎን መሠረታዊ ለውጥ ማምጣት ያስችላል ያለውን «ከተረጂነት ወደ ምርታማነት» የሚል ንቅናቄ መተግበሩን ይገልጻሉ። ይህም ተረጂው ማህበረሰብ አምራች እንዲሆንና በራሱ ታግሎ ከጠባቂነት አስተሳሰብና ተግባር እንዲወጣ ያለመ መሆኑን ያስረዳሉ። በዚህም በርካታ ተረጂዎች የተፈጠረላቸውን ምቹ ሁኔታ ተጠቅመው ከጠባቂት መውጣት እየቻሉ ቢሆንም የተረጂነትና የጠባቂነት አስተሳሰቡ ስር የሰደደ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሀገሪቱ ካቀደችው ግብ አንፃር በሚፈለገው ፍጥነትና መጠን ሽግግሩን ማፋጠን ያስፈልጋል ባይ ናቸው።

ወይዘሮ ሰዒዳ ከድር በግብርና ሚኒስቴር የምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት አማካሪ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፤ የገጠር ምግብ ዋስትና ፕሮግራም በ1997 ዓ.ም ከተጀመረ ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል። ዘንድሮ በመገባደድ ላይ ያለውን ጨምሮ በአምስት ምዕራፎች የመርሃ-ግብሩ ትግበራ ሽፋኑን በማሳደግ የተጠቃሚዎችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻልና ለመለወጥ የሚያስችሉ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል። በተለይም በአምስተኛው ምዕራፍ ፕሮግራሙ በአስር ክልሎች እና አንድ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ 7ነጥብ9 የሚልቁ ተጠቃሚዎችን በማቀፍ የሚተገበር ነው። በመሆኑም በፕሮግራሙ የመጀመሪያ ዓመት ላይ ማህበረሰቡን ባሳተፈ መልኩ የልየታ ሥራ ተሠርቷል። በዚህም አሰራር የድሃ ድሃ የሆኑ ቤተሰቦች ፍትሐዊ በሆነ የልየታ አሰራር ተለይተው የፕሮግራሙ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል።

ማሻሻያዎች እና አዳዲስ የአሠራር ሥርዓቶችን በማዘመንና በማስፋፋት ለመተግበር ያለው ጥረትና ቁርጠኝነት እንዳለ ሆኖ በትግበራው ሂደት የተለያዩ ችግሮች እንዳጋጠሙት ይጠቀሳል። አማካሪዋ እንደሚሉትም፤ በፕሮግራሙ ዲዛይን መሠረት ከለጋሾች መቅረብ የሚገባው ሀብት ላይ ከፍተኛ መዘግየትና የገንዘብ መጠን መቀነስ፣ በተደጋጋሚ የሚከሰተው ድርቅ፣ ኮቪድና ግጭት ምክንያት ለልማት መዋል ያለበት ሀብት ወደ እለት ደራሽ ምላሽ መዞሩና የተጠቃሚዎችን ጥሪት ማመናመኑ መርሃ-ግብሩ በተሳካ ሁኔታ እንዳይተገበር እንቅፋት ከሆኑ ጉዳዮች ዋነኞቹ ናቸው።

በተጨማሪም የዋጋ ንረት፣ በቤተሰብ ደረጃ የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎችን ኑሮ እንዲሻሻል ከማድረግ አንፃር ለልማት ሊውሉ የሚችሉ ያገገሙ ተፋሰሶችን ወደ ልማት ለማስገባት የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆን፤ በቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ የሥራ ዘርፍ የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች በተለያዩ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ በመሳተፍ ተጨማሪ ገቢና ጥሪት በመፍጠር ከፕሮግራሙ እንዲመረቁ ከማድረግ አንፃር በቂ የብድር አቅርቦት አለመኖሩ በአፈፃፀም የተለዩ ክፍተቶች መሆናቸውን ያስረዳሉ። እንዲሁም «በየደረጃው የሚገኙ ባለድርሻ አካላት በኃላፊነት ተጠያቂነት መንፈስ ሥራቸውን አለማከናወን ክፍተቶች ታይተዋል» ይላሉ።

በሌላ በኩል የተረጂን ቁጥር እና የተረጂነትን ስሜት ወይም አመለካከትን መቀነስ እና አደጋን የሚቋቋም ማህበረሰብ መፍጠር መቻል የሀገሪቱ እድገት አንዱ መገለጫ ነው። በዚህ ረገድም በዘርፍ ላይ በሁሉም ረገድ ዘላቂና ቀጣይነት ያለው የግብርና ሽግግር በማምጣት ለዜጎቹ በቂ፣ ጥራትና ደህንነቱ የተጠበቀ የምግብ አቅርቦትን በማሻሻል የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እየተሠራ መሆኑን ወይዘሮ ሰዒዳ ያመለክታሉ። ፕሮግራሙ የኅብረተሰቡን የምግብ ክፍተት በማሟላትና በተለያዩ የዕድገት መርሃ-ግብሮች ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተሳትፎ በማድረግ ሊቆጠርና ሊታይ የሚችል ለውጦች እንዲመጡ አስተዋፅኦ አድርጓልም ባይ ናቸው።

ይሁንና ሀገሪቱ ካስቀመጠችው የተረጂነት ቅነሳ መርሃ-ግብር አንጻር ሲታይ የተረጂነት አመለካከትን በማስተናገድና እርዳታን በመጠበቅ የእድገት ግቦችን ማሳካት ከባድ መሆኑን ያስረዳሉ። እንዲሁም በርከት ያለ ቁጥር ያለው ተረጂ ማህበረሰብንም ይዞም ሀገሪቷ ያስቀመጣቸውን ራዕይ ማሳካት አዳጋች እንደሆነ ነው ያስረዱት።

ስለሆነም የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎችን በአካባቢው ባለው እምቅ ሀብትና ፀጋ ተጠቅሞ በልማት እንዲሳተፉ በማድረግ ኑሯቸውን ማሻሻልና ከፕሮግራሙም በስፋት እየተመረቁ እንዲወጡ፣ የጠባቂነት አመለካከቶች ተወግደው የትርፍ አምራችነት ስሜት በተጠቃሚ የማህበረሰብ ክፍል እንዲሰፍን ማድረግ ተጠባቂ ሥራ እንደሆነ አማካሪዋ ይናገራሉ። በዚህ ረገድ ጉዳዩ የሚመለከተው አካል በቅንጅት የመሥራት ባህልን ማጎልበት እንደሚገባቸው ጠቅሰው፤ «በኃላፊነት፣ በቁርጠኝነትና በተጠያቂነት መንፈስ መሥራት ያስፈልጋል» ይላሉ። ይህንንም ለማረጋገጥ በክልል፣ በዞን፣

በወረዳና በቀበሌ የሚታቀዱ እና የሚተገበሩ ሥራዎች መኖራቸውና የቁልፍ አመላካቾች አፈጻጸሞችን በየጊዜው አፈጻጸማቸውና ውጤታቸው እየተገመገመ ለውጥ ለማምጣት መሥራት ግድ እንደሚል ነው ያስገነዘቡት።

ዶክተር ታደለ በበኩላቸው እንደሚናገሩት፤ ከሁሉ በፊት ከተረጂነት አስተሳሰብ እንዲላቀቁ የሰውን ንቃተ ህሊና መገንባት ያስፈልጋል። 'ማምረትና ራሴን መቻል እችላለሁ፤ ከራሴ አልፎ ለሌሎች እተርፋለሁ' የሚል አስተሳሰብ መፍጠር ይገባል። ለዚህ ደግሞ የመማሪያ መድረኮች ማዘጋጀት ይጠይቃል። ግንዛቤ ከመፍጠር ጎን ለጎን ተረጂዎችን ወደ ልማት ለማስገባት ወሳኝ የሆኑ እንደ መሬት፣ የብድር አገልግሎት፣ ግብዓትና መሰል ድጋፎች በበቂ ሁኔታ መመቻቸት ይኖርባቸዋል። በተጨማሪ ኢጋር የውጭ ድርጅቶች ችግሩ ሲፈጠር ብቻ እሳት ከማጥፋት በዘለለ መሠረታዊ ችግሮቻችንን በዘላቂነት መፍታት የሚያስችሉ ሥራዎችን እንዲሠሩ የተቀናጀ የማስተባበር ሥራ መሠራት አለበት።

«ችግሩን የለየ፣ ከአጭር እስከ ረጅም ጊዜ መፍታት የሚያስችል እቅድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል» የሚሉት ዶክተር ታደለ፤ በአጭር ጊዜ መጀመሪያ የህይወት አድን ሥራዎች ላይ ማተኮር፤ በሁለተኛ ደረጃ ከተረጂነት እንዲላቀቁና ወደ ልማት እንዲገቡ በማድረግ እሴት መገንባት ያስፈልጋል። ጎን ለጎንም 'እችላለሁ' የሚለውን አስተሳሰብ እንዲያሳድጉ ንቃተ ህሊናቸውን ማሳደግ ወሳኝ ነው።

በተጨማሪም በየአካባቢው ያለውን እምቅ አቅምና የተፈጥሮ ሀብት በመጠቀም ከተረጂነት እንዲወጡ ማድረግ እንደሚገባ ይናገራሉ። ለዚህም በዋናነት የክልል መንግሥታት ኃላፊነት ወስደው ያሉትን ሀብቶች በመለየትና ጥቅም ላይ ማዋል በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ መሥራት ይገባቸዋል ይላሉ። አብነት አድርገውም «ደቡብ ላይ እንሰትን ለምግብ ዋስትና ይጠቀሙበታል፤ ሆኖም በተመሳሳይ አግሮኢኮሎጂ ያላቸው አካባቢዎች ላይ ሲጠቀሙበት አናይም፤ በመሆኑም አንድ አካባቢ ያለውን ብቻ ሳይሆን ከሌላ አካባቢ ተሞክሮ መውሰድ ያስፈልጋል» ይላሉ። ይህንን ሥራ ከልማታዊ ሴፍትኔት መርሃ-ግብሩ ጋር ማገናኘት እንደሚገባም ነው የተናገሩት።

ለረጅም ጊዜ የቆዩትን የኅብረተሰብ ክፍሎች በአንድ ጊዜ ማላቀቅ እንደፈተና ሊታይ እንደሚችል አንስተው፤ የኅብረተሰቡን ንቃተ ህሊና የማሳደጉ ሥራ ከፍተኛ ትኩረት እንደሚገባው ያስገነዝባሉ። በተጨማሪም ዓለም አቀፍ የርዳታ ድርጅቶች ርዳታን አሳቦ እጅ በመጠምዘዝ ሀገራዊ ልዕልናን የሚዳፈሩና ፖሊሲን የመሻር ፍላጎት ሊኖራቸው ስለሚችል ተቀራርቦ በድርድር መፍታት እንደሚጠይቅ ይናገራሉ። « እነዚህን ስጋቶች በማስወገድ ከተረጂነት የተላቀቀ አልሚ ማህበረሰብ መፍጠር ከተቻለ ኢትዮጵያ የረሃብ ተምሳሌት ተደርጋ በዓለም አደባባይ የምትታወቅበት ገፅታ ይቀየራል» ይላሉ። ኢትዮጵያ እንደሀገር በየትኛውም መድረክ ላይ ራሷን ማስከበርና የመከላከል አቅሟ ይጎለብታል።

ኢትዮጵያ ከነፋስ ኃይል 1 ነጥብ 35...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በተለይም የውሃ መጠን በሚቅንስበት የበጋ ወራት የውሃ ኃይል ማመንጫዎችን ክፍተት ከመሙላት አንጻር አስተዋጽኦ እያበረከቱ እንደሚገኙ አስታውቀዋል።

በአሁኑ ሰዓት ከሀገሪቱ አጠቃላይ የማመንጨት አቅም ውስጥ የንፋስ ኃይል 7 ነጥብ 14 በመቶ ድርሻ እንዳለው ያመለከቱት አቶ ፍሰሃ፤ በ2016 በጀት ዓመት የ3 ነጥብ 32 በመቶ አስተዋጽኦ በማበርከት ለውሃ ኃይል ማመንጫዎች ተጨማሪ አቅም እንደፈጠረ አስታውሰዋል።

ተቋሙ በአሁኑ ወቅት ከአሸጎዳ 120 ሜጋ ዋት፣ ከአዳማ-1 51 ሜጋ ዋት፤ እንዲሁም ከአዳማ-2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ 153 ሜጋ ዋት፤ በድምሩ 324 ሜጋ ዋት በማመንጨት ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

120 ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም ያለው የአይሻ-2 እና 100 ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም ያለው የአሰላ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች በግንባታ ላይ እንደሚገኙም ጠቅሰዋል። የአይሻ-2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ግንባታው ሳይጠናቀቅ በአሁኑ ወቅት 80 ሜጋ ዋት እያመነጨ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

300 ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም ያለው የንፋስ ኃይል ማመንጫ በሶማሌ ክልል አይሻ ወረዳ ለመገንባት አሜአ ፓወር ከተሰኘ የተባበሩት አረብ ኤምሬቶች ኩባንያ ጋር ስምምነት ስለመፈረሙ አስታውሰዋል። ፕሮጀክቱ በመንግሥት እና በግል አጋርነት ማሕቀፍ የሚገነባ ትልቁና የመጀመሪያው የንፋስ የኃይል ማመንጫ ኢንቨስትመንት እንደሆነም አቶ ፍሰሃ አስረድተዋል።

በአሁኑ ጊዜ ለንፋስ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ግንባታ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶና የሕግ ማሕቀፍ ተዘጋጅቶ ዘርፉ ለግል አልሚዎች ክፍት መደረጉ መደላድል የፈጠረ ስለመሆኑ ጠቅሰው፤ የሀገር ውስጥም ይሁን የውጭ ባለሀብቶች ዘርፉን በማልማት ሥራ ቢሰማሩ የኃይል አቅርቦትን በማሳደግ ለሀገር ልማትና ለውጭ ምንዛሪ ግኝት በማዋል እድገትን ማስቀጠል እንደሚቻል አመልክተዋል።

በሁለትዮሽና ቀጣናዊ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ከጅቡቲ ፕሬዚዳንት ኢስማኤል ኦማር ጌሌ እና ከውጭ ጉዳይ እና ዓለም አቀፍ ትብብር ሚኒስትር ማህሙድ አሊ ዩሱፍ ጋር በሁለትዮሽ እና በቀጣናዊ የፖለቲካና የደህንነት ጉዳዮች ዙሪያ በትብብር መሥራት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ መወያየታቸውን ገልጸዋል።

በንግድ ጉዳዮች፣ በወደብ አጠቃቀም እና በወቅታዊ ቀጣናዊ ደህንነት ጉዳዮች ዙሪያም መምከራቸውን ለአብነት ጠቅሰዋል።

በአጠቃላይ ከባለሥልጣናቱ ጋር ገንቢ እና ፍሬያማ ውይይት እንዳደረጉ አመልክተዋል።

ኢትዮጵያና ጅቡቲ በባቡር፣ በወደብና መሠረተ ልማት መስኮች ዘመናትን የተሻገረ ታሪካዊ ወዳጅነት ያላቸው ሀገራት መሆናቸውንም ጠቁመዋል። ሀገራቱ በጣም ልዩ እና ጠንካራ ትብብር እንዳላቸውም ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ እና ጅቡቲ መደበኛ ዲፕሎማሲያዊ

ጌዲዮን ጢሞቲዎስ (ዶ/ር)

ግንኙነት እ.አ.አ በ1984 እንደተጀመረ መረጃዎች ያመለክታሉ።

ርዕሰ አንቀፅ

ታሪክን ያደሰ፣ የሀገር ገጽታን እና የቱሪዝም ጠቀሜታን ታሳቢ ያደረገ መልካም ተግባር!

ኢትዮጵያ እንደ ሀገር፤ ኢትዮጵያውያንን እንደ ሕዝብ ከሦስት ሺህ ዘመናት የተሻገረ ታሪክ ያላቸው ባለታሪኮች ናቸው ሲባል፤ የታሪካቸውን ተሰናስሎ፣ የሥርዓተ መንግሥቱን ቀጣይነት፣ የባህልና የቱሪዝም አቅም የሚሆኑ ተፈጥሮም የሕዝቦች የጥበብ አሻራም የቸሯቸው አያሌ መገለጫዎች ያሏቸው ጭምር ስለመሆናቸው የሚገለጥበት የተረከ ውቅር አለ።

ይሄ የተረከ ውቅር ታዲያ፣ በተረት ተረት የተወረሰ ሳይሆን፤ በሚገለጥ እውነት፣ በሚጨበጥም ሕያውነት የሚረጋገጥ ነው። ይሄ ተጨባጭነቱ ደግሞ ተራኪዎችን ልበ ሙሉ፤ ተግባሪዎችንም ባለ ዐሻራ ትውልድ ያደረገ፤ ከትናንት እስከ ዛሬም በትውልዶች ቅብብሎሽ ውስጥ ደምቆ የዘለቀ ከፍታን ያጎናጸፈም ነው።

ይሄ የኢትዮጵያ እውነትም ሆነ የኢትዮጵያውያን የኑሮ ዐሻራ ታዲያ፤ አንድም እውነቱን የመግለጥ ስንፍና እና እውነትን ያለመረዳት አላዋቂነትን ታክኮ፤ ሁለትም እውነትን በመግለጥና ታሪክን በማደስ ውስጥ የትናንቱ ታላቅነት የዛሬውን ግብር ያሳንሳል ከሚል ታሪክ ጠል ምልከታ ተሹበቦ ሳይገለጥ ተዳፍኖ ኖሯል።

ከ2010ሩ ሀገራዊ ለውጥ ማግስት፣ በተለይም እንደ ሀገር እየተተገበረ ከሚገኘው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሪፎርም ጋር በተያያዘ፤ እንደ ሀገር ያሉ አቅሞች ተሰባስበውና ተደምረው የብልፅግናው ጉዞ ማሳለጫ እንዲሆኑ የግድ አለ። እናም ሀገር ያላት አቅምና ሀብት፣ እውቀትና ታሪክን የመሳሰሉ የማደጊያና የመበልጸጊያ መንገዶች ሁሉ መፈተሽ ጀመሩ።

ለምሳሌ፣ እንደ ሀገር ለሚፈለገው ሀገራዊ የልማት ግብ፤ አንድ መንገድ (ለምሳሌ ግብርናው) ላይ ብቻ ተንጠልጥሎ ማሳካት እንደማይቻል ይታመናል። ለዚህም፣ ማዕድን፣ ዲጂታላይዜሽን፣ ቱሪዝም፣ ግብርናን የመሳሰሉ ዘርፎች ላይ ያሉ አቅሞችን መደመር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

በመሆኑም በአስር ዓመቱ እውን እንዲሆን ለሚጠበቀው ግብ አቅም ሆኖ ከተመረጡ ዘርፎች አንዱ ቱሪዝም ነው። እንደ ሀገር ደግሞ የቱሪዝሙን አቅምነት ከፍ የሚያደርጉ አያሌ ሀብቶች አሉ። ይሁን እንጂ እንደ ሀገር ቀደም ሲል እነዚህን ሀብቶች ከመለየትና ከማልማት፣ ከመጠበቅና የኢኮኖሚ አቅም ከማድረግ አኳያ እዚህ ግባ የሚባል ሥራ ሳይሠራ ቆይቷል።

ከለውጡ ማግስት ግን አንዱ ትኩረት ተደርጎ ከተሠራባቸው ጉዳዮች መካከል እነዚህን የቱሪዝም አቅሞች የመለየት፣ የማልማትና የገቢ አቅም የማድረግ ጉዳይ ነው። በዚህ ረገድ ሀብትነታቸው ሳይሆን የቆሻሻ ማዕከል ሆነው የመታየት እድላቸው ከፍ ብሎ የነበሩ ከአዲስ አበባ እስከ ክልል ያሉ ሥፍራዎች፤ ከቤተ መንግሥቱ ቅጥር እስከ ወንዝ ዳርቻዎችና ጥቅጥቅ ደኖች ያሉ ገጽታዎችን መቀየር ተችሏል።

በተለይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ባላቸው ከፍ ያለ እይታ ምክንያት፤ በገበታ ለሸገር ጀምረው እስከ ገበታ ለትውልድ በዘለቀው መንገዳቸው በርካታ ሀብቶችን ለይቶ ማልማት እና ታሪክንም፣ ገጽታንም፣ የቱሪዝም አቅምንም መግለጥ፤ ዘርፉንም የኢኮኖሚው አቅም ማድረግ ተችሏል።

የአንድነት ፓርክ፣ የወዳጅነት አደባባይ፣ የእንጦጦ ፓርክን የመሳሰሉት በገበታ ለሸገር፤ ጎርነራ፣ ኮይሻ እና ወንጪ ደንዲን የመሳሰሉት በገበታ ለሀገር፤ እንዲሁም ሌሎች በገበታ ለትውልድ ማሕቀፍ ተይዘው እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎች ለዚህ ሕያው ምስክር ናቸው።

ከሰሞኑ ነባር ማንነቱን በአዲስ ገጽታ ይዞ ተደማሪ ድምቀትና ታላቅነትን እንዲገልጥ ሆኖ የተሰናዳው የብሔራዊ ቤተ መንግሥት እድሳት ሥራም የዚህ የሀገርን ታሪክ የማክበር፣ ገጽታዋንም የመግለጥ፣ የቱሪዝም ዘርፉንም ከፍ ወዳለ ምዕራፍ የማሸጋገርና ዘርፉን የኢኮኖሚው አዕማድ የማድረግ ተግባር ማሳያ ነው።

ምክንያቱም፣ በብሔራዊ ቤተ መንግሥቱ ውስጥ ለጥቂቶች እይታ ብቻ (ያውም ጥቂት ገጹን) ተገድቦ የኖረውን ታሪክና ሀብት፤ ለሕዝብ እይታ እንዲበቃ ያደረገ ሆኗል። ኢትዮጵያ የታሪኳን መንገድ እንድትገልጥ፤ የሥልጣኔዋን ጣሪያ እንድታሳይ፤ የሥርዓተ መንግሥቷን ጉዞ እንድትናገር፤ የነጻነትና አርዓያነት መንገዷን እንድታስረዳ የሚያስችልም ነው።

ይሄ ደግሞ ታሪክን የሚወድድ፣ በታሪኩ የሚኮራ፣ ታሪኩንም የሚያውቅ፣ ለታሪክና ለባለታሪኮችም ክብርና ፍቅር ያለው፤ በጥቅሉ ኢትዮጵያን የሚወድድ፣ ኢትዮጵያውያንንም በሚመጥናቸው ልክ ለማኖር የሚተጋ መሪና ትውልድ እሳቤና ተግባር ነው። የተዳፈነውን የሚገልጥና የቱሪዝም መንገዱን ብርሃን ከሚያደርግ ትውልድ፤ አቧራውን አራግፎ ደምቆ የሚታይ ዐሻራን ከሚያኖር መሪ፤ የታሪክ ከፍታን በመግለጥ ውስጥ ከፍ ያለ ታሪክን ለማኖር ከሚታትር መንግሥት ቅን እሳቤ ተወልዶ የተተገበረ ታላቅ ሥራ ነው።

ለዚህም ነው የተደበቁት አቅሞች እየተገለጡ፤ በከፉ ትርክት የተዳፈኑ ከፍታዎች ዳግም እየታደሱ፤ የግለሰብና ቡድኖች የግል ሀብት መስለው ይታዩ የነበሩ የወል ሀብቶች ዳግም የሕዝብ ሀብትነታቸውን እንዲጎናጸፉ እየሆኑ ያሉትታሪክን ያደሰ፣ የሀገር ገጽታን እና የቱሪዝም ጠቀሜታን ታሳቢ ያደረገ መልካም ተግባር! ከዚህ አኳያ የለውጡ ማግስት መንገድን ከፍ አድርገው ካሳዩት ተግባራት መካከል አንዱ የሆነው የብሔራዊ ቤተ መንግሥት እድሳትም ታሪክን ያደሰ፣ የሀገር ገጽታን እና የቱሪዝም ከፍታን ያቀናጀ መልካም ተግባር ነው!

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ደህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

ነፃ ሃሳብ

ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው የዲጂታል አድራሻ ሥርዓት

በቀምሳቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የከተማዋን የዲጂታል አድራሻ ሥርዓት ለመዘርጋት ከስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ጋር ሰሞኑን ስምምነት ተፈራርሟል። ከተሞች ስማርትና ዲጂታል እየሆኑ ባለበት በዚህ የቴክኖሎጂ ዘመን ሥርዓቱን የመዘርጋቱ ሒደት ቢዘገይም ዛሬም አረፈደምና ይበል የሚያሰኝ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። በነገራችን ላይ የቢሾፍቱ ከተማ ባለፈው ዓመት ይሄን ሥርዓት በመዘርጋት መዲናችንን ቀድማታለች።

ተቋማት፣ ቦታዎች እንዲሁም ቤቶችና የመሳሰሉት የት እንደሚገኙ በዲጂታል መልኩ በየፈርጁ ያልተመዘገቡባት ኢትዮጵያ የአድራሻ ሥርዓቷን ባለማዘመንዋ የተነሳ የይዘታ መረጃዎችን በአግባቡ ለማስተዳደር ስትቸገር መቆየቷ ይነገራል፡፡ይህ መረጃ በአግባቡ ባለመሰነዱ የተነሳም ሀገሪቱ የኢ ኮሜርስና የኢ ሰርቪስ አገልግሎቶችን ለመስጠት የምታደርገው ጥረት ብቻ ሳይሆን የመኖሪያ ቤቶችና የትላልቅ ተቋማት እንዲሁም የትራፊክ እንቅስቃሴ መረጃዎችን ማግኘት አዳጋች ነበር፡፡

በሀገራችን በየከተሞች ያለውን እድገትና መስፋፋት ተከትሎ ከቦታ ወደ ቦታ ለመንቀሳቀስ በቂ አድራሻ ማግኘት አስቸጋሪ ነው። ሌላው ቀርቶ ችግር ተፈጥሮ ለእርዳታ የሚንቀሳቀሱ የእሳት አደጋ መኪናና ተጎጂዎችን የሚያነሱ አምቡላንሶች ከተጠሩበት ቦታ የሚደርሱት ከብዙ ምሬት በኋላ ነው። ያደጉት ሀገራት ከተሞች የተጠናከረ የአድራሻ ሥርዓት ስላላቸው ዘመኑ ያፈራቸው ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ከቦታ ወደ ቦታ በቀላሉ ለመንቀሳቀስ እየተጠቀሙባቸው ይገኛል። በተጨማሪም የየከተማ አስተዳደሮች በከተሞቻቸው ያሉ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን አድራሻ በመስጠት በቀላሉ ለማስተዳደር እና የማህበረሰባቸውንም የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ምቹ እና ወጪ ቆጣቢ ለማድረግ አስችሏቸዋል።

የአካባቢውን፣ የመኖሪያ ቤቱን፣ የሥራ ቦታውን በቀላሉ ለተገልጋዮች ለመግለጽ፣ የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ ለማግኘት፣ ለወዳጅ ዘመዶቹ እና ለሌሎች አካላት በቀላሉ ያለበትን አድራሻ ለማመላከት ወይም ለመጠቆም የሚያስችል ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ እና ዓለም አቀፍ ተሞክሮን መሰረት ባደረገ መልኩ የብሔራዊ ዲጂታል አድራሻ ሥርዓት ሥርአት ደንብ እና መመሪያ ተዘጋጅቷል።

የዲጂታል አድራሻ ሥርዓት መዘርጋት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው ነው። ግለሰቦች የእለት ከእለት እንቅስቃሴዎቻቸውን ቀላል ከማድረግ ጀምሮ የተቀላጠፈ የመሠረተ ልማት ዝርጋታና ጥገና አገልግሎት ለማግኘት፣ ፈጣን የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ እና ቅድመ ማስጠንቀቂያ ለመስጠት፣ መንግሥታዊ አገልግሎቶችን ለማዘመን፣ የዲጂታል ኢኮኖሚን ሥርዓት ለመዘርጋትና እውን ለማድረግ፤ የኤሌክትሮኒክ ግብይቶችን (e-commerce) እና ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለማሳለጥና ለመደገፍ ዋነኛ መሠረት ሆኖ የሚያገለግል ነው።

የዲጂታል አድራሻ ሥርዓት ማለት መሬት ላይ የሚገኙ ማናቸውንም ነገሮች ህንጻዎች/ቤቶች፣ መንገዶች፣ መሠረተ ልማቶች፣ ክፍት ቦታዎች፣ ፓርኮች፣ መዝናኛና መናፈሻ ቦታዎች እና ሌሎች ነገሮችን መገኛ (location) በካርታ ላይ የማስፈር እና ዜጎች በቀላሉ አድራሻውን እንዲያገኙ በማድረግ የትራንስፖርት ወጪያቸውን እንዲቀንሱና ፈጣን እና ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስችል ሥርዓት ነው።

ይህ ሲተገበርም እያንዳንዱ መሬት ላይ ያለው ነገር ከጀርባው የጂ.ኤን.ኤስ.ኤስ (GNSS በተለምዶ GPS) መረጃ የያዘ የራሱ ልዩ መለያ ቁጥር እንዲኖረው ይደረጋል። በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ አድራሻ ለእያንዳንዱ ቤት፣ መንገድና ሌሎች በመሬት ላይ ያሉ ንብረቶች የሚሰጥበት ሥርዓት ነው። ቀደም ባሉት ጊዜያት እንዲሁም አሁንም አብዛኛው ማህበረሰብ የተለያዩ ተቋማትን አገልግሎት ለማግኘት፣ የተለያዩ ግብይቶችን ለመፈጸም፣ ወዳጅ ዘመድ ለመጠየቅ፣ በየመንገዱ እየቆመ እና ሰዎችን እየጠየቀ የሚሄድበት ሁኔታ ያስቀራል፡፡ይህን እውን ለማድረግ ይረዳ ዘንድ ራሱን የቻለ መመሪያ ጸድቆ ወደ ሥራ ተገብቷል።

በሀገራችን በየከተሞች ያለውን እድገትና መስፋፋት ተከትሎ ከቦታ ወደ ቦታ ለመንቀሳቀስ በቂ አድራሻ ማግኘት አስቸጋሪ ነው

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት የመንግሥትና የሕዝብ መሆኑን በግልጽ ደንግጓል፡፡ ከዚህ በመነሳት የከተማ መሬት ምዝገባን ለማሳለጥ የእያንዳንዷን ቁራሽ መሬት አድራሻ እና ቁራሽ መሬቱም ለምን አገልግሎት እየዋለ መሆኑን በአድራሻው ለማረጋገጥ የሚረዳ ሥርዓት ተግባራዊ እንዲደረግ በመንግሥት ተወስኗል፡፡

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

ነፃ ሃሳብ

ጽህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ሳጋ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኃን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው...

ከገጽ 5 የዘረ

ከዚህ አኳያ ከተሞች መሬትን በዘመናዊ መንገድ ለማስተዳደር በተለይም የአድራሻ ሥርዓት ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡ዘመናዊ የአድራሻ ሥርዓት በከተሞች ያሉ መንገዶችን እና የአድራሻ ታፔላዎችን ዝርጋታ እና ሌሎች በመሬት ላይ ያሉ ቋሚ ንብረቶችን ለማመላከት የሚያስችል ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ የአድራሻ ሥርዓት በማደግ ላይ ላሉ የከተማ ነዋሪዎች ዘመናዊ የኑሮ ሁኔታ እንዲፈጠር እገዛ የሚያደርግ እና መልካም አስተዳደርን ለመገንባት የሚያግዝ አስተዳደራዊና ማህበራዊ አገልግሎቶችን በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግ አስተዋጽኦው የጎላ ነው፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአሁኑ ወቅት ለከተማዋ አጠቃላይ የአድራሻ ሥርዓት እየተዘረጋ ይገኛል፡፡ የአድራሻ ሥርዓቱ በዋነኛነት የመንገድ ስያሜ ወይም የመንገድ መለያ ቁጥርና የቤት ቁጥርን በማገናኘት የሚከናወን ሲሆን፤ ከሥርዓቱ ጋር የሚጣጣም የቤት ቁጥር መስጠት ተገቢ ሆነዋል፡፡ ያለፈው መንግሥት በጊዜው ለነበሩ ቤቶች የቤት ቁጥር ከሰጠ በኋላ የተገነቡ በርካታ ቤቶች ስላሉና የቤት ቁጥር ሊሰጣቸው ስለሚገባ፤ በከተማው የልማትና የመልካም አስተዳደር ሥራዎች የተቀላጠፈ ለማድረግ በተደጋጋሚ በተደረገው አስተዳደራዊ የመዋቅር ለውጥ ምክንያት የቀበሌዎች መቀላቀልና መከፈል ስለተፈጠረ የቤት ቁጥር ድግግሞሽንና ምስቅልቅልነትን የፈጠረ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ይህ ደግሞ ከተማዋን ከማዘመን አንፃር ቀድሞ የነበረው የቤት ቁጥር አሰጣጥ ምቹ ሆኖ ስላልተገኘ፤ በተጨማሪም ከዚህ ቀደም የቤት ቁጥር በምን ሕግ መሠረት ሲሰጥ እንደነበረ ወጥነት ያለው መረጃ ባለመኖሩና እሱን ተከትሎ መስጠት ስላልተቻለ እንደገና ከአድራሻ ሥርዓቱ ጋር በተጣጣመ መልኩ የቤት ቁጥር መስጠት አስፈልጓል፡፡ ስለዚህ የተቀናጀ የመሬት መረጃ ማዕከልና የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 64/2011 ዓ.ም ከእነ ሙሉ መብትና ግዴታ የተዋሐዱ በመሆናቸውና የአድራሻ ሥርዓት ለመዘርጋት፣ ለማስተዳደር የቤት ቁጥር ለመስጠት ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ፤ በፌዴራል የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር በተዘጋጀው የኢትዮጵያ ከተሞች የአድራሻ ሥርዓት ስታንዳርድን መሰረት በማድረግ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

መመሪያውን የማውጣት አስፈላጊነት

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ የአድራሻ ሥርዓት ትግበራ በመዘርጋት ሂደት ላይ

ይገኛል፡፡ የአድራሻ ሥርዓቱ በዋነኛነት ዋና ዋና አደባባዮችንና የመንገድ ዓይነቶችን

መሰረት በማድረግ በጂኦ-ኮዲንግ ፅንሰ ሃሳብ መሰረት አድርጎ የመንገድ ስያሜ ወይም

የመንገድ መለያ ቁጥርና የቤት ቁጥርን በማቀናጀት የሚከናወን ሲሆን ከሥርዓቱ ጋር

የሚጣጣም አዲስ የቤት ቁጥር በከተማ ደረጃ ወጥ በሆነ መንገድ ለመስጠት ያስችላል፡፡

መመሪያው ለከተማው የሚከተሉት ጥቅሞች ይኖሩታል።

1. የቋሚ ንብረት ምዝገባ በማካሄድ ለዜጎች የንብረት ዋስትና ለመስጠት መንግሥት የሚያደርገውን የንብረት ምዝገባ ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ ግብዓት በመሆን ሂደቱንም ይበልጥ ለማፋጠን ይረዳል፣
2. የመንገድ ቁጥርና የቤት ቁጥርን በማስተሳሰር ለዘመናዊ የአድራሻ ሥርዓት ወይንም ጂኦ-ኮዲንግ ሲስተም በመፍጠር ዓለም አቀፍ ደረጃውን ያሟላች ከተማ ለማድረግ፡፡
3. የከተማዋን ዕድገት መሰረት ያደረገና ዓለም አቀፍ ደረጃውን ያሟለና ለነዋሪዎቿ ምቹ ከተማ ለመፍጠር እንዲቻል ከዘመናዊ የአድራሻ ሥራ ጋር አብሮ ሊሄድ የሚችል የቤት ቁጥር በስታንዳርዱ መሰረት ለመስጠት፣
4. የከተማው ነዋሪ የመብራት፣ የውሃ፣ የኤሌክትሪክ፣ የፖስታ፣ የእሳት አደጋ፣ የፖሊስ እና ሌሎች ኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊና ማህበራዊ አገልግሎቶችን በቅልጥፍና እንዲያገኝና የግል ሴክተሩም በልማት ሥራው ላይ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር፣
5. ዘመናዊ የአድራሻ ሥርዓት እንዲኖራት በማድረግ ቋሚና የማይደጋገም የቤት ቁጥር በመስጠት ወደ አገልግሎት በማስገባት ከመታወቂያ ወረቀት ዕደላ ጋር ተያይዞ የሚፈጠሩ ሕገ-ወጥ አሠራሮች ለመከላከል ያግዛል። በነገራችን ላይ የቢሾፍቱ ከተማ ዲጂታል የአድራሻ ሥርዓትን ወደ ሥራ በማስገባት ፋና ወጊ ናት ማለት ይቻላል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር በለጠ ሞላ (ዶ/ር) ባለፈው የቢሾፍቱ ከተማን ዲጂታል የአድራሻ ሥርዓት መርቀው በከፈቱበት ወቅት፤ “የአድራሻ ሥርዓት ሳይኖር የዲጂታል ኢኮኖሚን መገንባት አይታሰብም” ማለታቸው ይታወሳል፡፡ በማያያዝም መንግሥት የዲጂታል ኢኮኖሚውን ለመገንባት ስትራቴጂ ነድፎ እየሰራ እንደሚገኝ፤በዚህም የዲጂታል መታወቂያ፣ የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎቶች እንዲሁም የዲጂታል አድራሻ ሥርዓት ዝርጋታ ማሳያዎች ናቸው፡፡

በ73 የኢትዮጵያ ከተሞች ተግባራዊ ለማድረግ እየተሠራ ያለው የዲጂታል አድራሻ ሥርዓት “(eDAS)”አስተዳደራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎቶችን ቀልጣፋ ለማድረግ፣ የከተሞችን ምቾትና ደህንነት ለማረጋገጥ እንዲሁም ዘላቂ የልማት ግቦችን ተግባራዊ ለማድረግ ዓይነተኛ ሚና እንደሚኖረው ጠቅሰዋል፡፡ የዲጂታል አድራሻ ሥርዓቱን ያለማው የስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ነው፡፡ የስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ አብዲሳ ይልማ በበኩላቸው፤ በቢሾፍቱ ከተማ የተገኘውን ልምምድ በመጠቀም ፕሮጀክቱን በተለያዩ ከተሞች ተግባራዊ ለማድረግ ከተማ አስተዳደሮች አስፈላጊውን ዝግጅት እያደረጉ እንዲቆዩ በወቅቱ አሳስበዋል፡፡

ነገርን ነገር ያነሳዋል እንዲሉ የአሊባባ እህት ኩባንያ አሊኤክስፕረስ ይህ የዲጂታል የአድራሻ ሥርዓት ከመዘርጋቱ በፊት ኢትዮጵያ ገብቶ ሥራ ጀምሯል። የኤሌክትሮኒክ ግብይት(e-commerce)ያለ ዲጂታል የአድራሻ ሥርዓት ማሰብ ከባድ ነውና በአጭር ጊዜ ተጠናቆ ወደ ሥራ ሊገባ ይገባል። ስለ አሊባባ ካነሳሁ አይቀር ትንሽ ልበል።

በዓለማችን በአንድ ቀን በቻይና የላጤዎች ቀን singles day በኤሌክትሮኒክ ግብይት አሊባባ ያስመዘገበውን ሽያጭ አማዞንና ኢቤይ ተደምረው በቫላንታይስ ፣ በአዲስ ዓመት ፣ በጥቁሩ ሰኞ እና በሌሎች በዓላት ካስመዘገቡት ሽያጭ በላይ ነው። በአግባቡ ከተጠቀምንበት ከአሊባባ ጋር መሥራት በዓለም ገበያ ያለከልካይ የመቅዘፍ ያህል ነው። ለመሆኑ ጃክ ማ ማን ነው? ሰለሞን ሙሉጌታ ካሳ በebs ቴሌቪዥን የTeckTalk አዘጋጅ “ግርምተ ሳይቴክ” በተሰኘው ድንቅ መጽሐፉ “ዓለምን የቀየሩ የ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን 20 ምርጦች” በሚል ንዑስ ርዕስ እንዲህ ያስነብበናል።

“ … ‘ አሊ ባባ ’ የተሰኘው ግዙፍ የቻይና የቴክኖሎጂ ኩባንያ መስራችና ዋና ሥራ አስኪያጅ ከድህ ቤተሰብ በመስከረም 1964 ዓ.ም ተወለደ። በትውልድ ስሙ ማን ዩን በፕሮፌሽናል የስም አጠራሩ ጃክ ማ በመባል ይታወቃል። በበርካታ የህይወት ፈተና ያለፈው ጃክ ማ እንኳን ግዙፍ የሆነ የቴክኖሎጂ ኩባንያ ባለቤት እንደሚሆን ሊያስብ ቀርቶ በሂሳብ ትምህርት ደካማ እንዲሁም እስከጉልምስናው ኮምፒውተር ባለበት ድርሽ ብሎ አያውቅም። በወጣትነቱ በቱሪስት አስጎብኚነት ተሰማርቶ የነበረው ጃክ ማ በህይወቱ በርካታ ውድቀቶችን አስተናግዷል።

የኮሌጅ መግቢያ ፈተናን ሶስት ጊዜ ወድቆ በአራተኛው ነበር የተሳካለት። ኮሌጅ ገብቶ የተማረውም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ነበር። ከጨረሰ በኋላ ለ30 የተለያዩ መሥሪያ ቤቶች አመልክቶ ሳይሳካለት ቀረ። በአንድ “KFC” በሚባል ምግብን በርካሽ የሚሸጥ ምግብ ቤት በአነስተኛ ደመወዝ ለመቀጠር ከ24 ሥራ ፈላጊዎች ጋር አመልክቶ ሁሉም ሲቀጠሩ እሱ ብቻ ሳይሳካለት ቀረ። ለፖሊስነት ለመቀጠር ተወዳድሮም ወድቋል። “ተስፋ መቁረጥ ትልቅ ውድቀት ነው።” የሚለው ጃክ ማ በዚህ ሁሉ ፈተና እና ውድቀት ቢያልፍም እጁን አጣጥፎ አልተቀመጠም። ከብዙ ልፋትና ውጣ ውረድ በኋላ ተሳክቶለት በወር 12 ዶላር እየተከፈለው በእንግሊዘኛ ቋንቋ በመምህርነት ተቀጠረ።

በዚህ ከባድ ፈተና በማለፍ ላይ ሳለ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ በ1994 ዓ.ም ስለኢንተርኔት የሰማው። ከአንድ ዓመት በኋላ በተፈጠረለት መልካም አጋጣሚ ወደ አሜሪካ አቀና። በዚያም ስለኢንተርኔት አጠቃቀም መሰረታዊ ግንዛቤ እንዳገኘ ስለሀገሩ ቻይን ለማወቅ ጉጉት አድሮበት መረጃ ሲያስስ እንደሌሎች ሀገራት የደለበ መረጃ ማግኘት አለመቻሉ ቁጭት ፈጠረበት። በዚህ በመነሳሳት ከጓደኛው ጋር ስለ እናት ሀገሩ የተለያዩ መረጃዎችን የሚሰጥ ድረ ገጽ ፈጠረ። በጥቂት ሰዓታት የአብረን እንስራ ጥያቄዎች ከየአቅጣጫው ጎረፉለት።

በዚህ ጊዜ ነበር ጃክ የኢንተርኔትን ኃይል የተረዳው። ከባለቤቱ እና ከጓደኛው ጋር 20ሺህ የአሜሪካ ዶላር ወረት በማሰባሰብ በሚያዚያ 1995 ዓ.ም “ቻይና የሎ ፔጅን / chaina yellow page ” አቋቋመ። በሶስት ዓመቱ 800ሺህ ዶላር አተረፈ ። 1999 ዓ.ም ከ18 የሥራ ባልደረቦቹ ጋር በመሆን የዛሬውን “አሊ ባባ” መሰረተ። በጥቂት ወራት ውስጥም ከባለሀብቶች 25 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ አሰባሰበ። በ2005 ዓ.ም ያሁ / yahoo / አንድ ቢሊዮን ዶላር ኢንቨስት በማድረግ ከአሊባባ የ40 በመቶ ድርሻን ገዛ። ነጮች የተቀረው ታሪክ ነው ቢሉም የጃክ ማ ጉዳይ ከታሪክ በላይ ስለሆነ እንቀጥል።

በ2006 ዓ.ም አሊ ባባ በታዋቂው የኒዮርክ የአክሲዎን ሽያጭ / New York Stock Exchange / ለመጀመሪያ ጊዜ ለሕዝብ ሲቀርብ ነጮች Initial Public Offering / IPO / ይሉታል ። 25 ቢሊዮን ዶላር የተተመነለትን ሽርክና በመሰብሰብ ከአንጋፋ የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች ተርታ ተሰለፈ። በ2008 ዓ.ም የ463 ቢሊዮን ዶላር ግብይት አከናወነ። የቅርብ ጊዜ ተመኑም ከትሪሊዮን ዶላር በላይ እንደሆነ ይገመታል። ዛሬ ተአምረኛው ጃክ ማ ከ50 ቢሊዮን ዶላር በላይ የሚገመት ሀብት ባለፀጋ ነው። በዓለማችን በቁጥር አንድነት በሚታወቀው የአሜሪካው ሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን ለመከታተል 10 ጊዜ አመልክቶ ውድቅ እንዳልተደረገበት በኋላ ላይ ግን በከብር ጥሪ ተደርጎለት የከብር ተናጋሪ ለመሆን በቅቷል። ታዋቂውና ተነባቢው የTIME መጽሔት በ2009 ዓ.ም ከዓለማችን ተፅዕኖ ፈጣሪዎች አንዱ አድርጎ መርጦታል። …”

ሻሉም ! አሜን ።

በዓለማችን በአንድ ቀን በቻይና የላጤዎች ቀን singles day በኤሌክትሮኒክ ግብይት አሊባባ ያስመዘገበውን ሽያጭ አማዞንና ኢቤይ ተደምረው በቫላንታይስ፣ በአዲስ ዓመት ፣ በጥቁሩ ሰኞ እና በሌሎች በዓላት ካስመዘገቡት ሽያጭ በላይ ነው

ኢኮኖሚ

ሳይንስና ቴክኖሎጂ

ያለነዳጅና ሶላር የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያመነጨ ጀነሬተሮችን በታዳጊው

ወርቅነሽ ደምሰው

ተወልዶ ባደገበት የገጠር አካባቢ የኤሌክትሪክ ኃይል አልነበረም። ምንም እንኳን በልጅነቱ የኤሌክትሪክ ኃይል የሚባል ተጠቅሞ ባያውቅም የኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰጣቸውን ጥቅሞች ግን ጠንቅቆ ያውቃል፤ የተወለደበት አካባቢም የዚህ የኤሌክትሪክ ኃይል እንዲኖረው ሲመኝ ኖሯል። ምኞት ብቻ ሳይሆን በተግባር ሆኖ ማየት ይፈልግም ነበር።

የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ሲሆን ወደዚህ መንገድ የሚያመራውን ሀሳብ አገኘ። ሀሳቡ እውን ሆኖም ሁለት አይነት ጀነሬተሮች ለመስራት የቻለው ይህ የፈጠራ ባለሙያ ተማሪ አብዱራህማን ከድር ይባላል።

አብዱራህማን የ10ኛ ክፍል ተማሪ ነው። ምንም አይነት የነዳጅም ሆነ የሶላር ኃይል ሳይጠቀሙ ኃይልን የሚያመነጩ ሁለት አይነት ጀነሬተሮችን መስራት የቻለው። ጀነሬተሮቹ 60ና 150 ዋት ኃይል ማመንጨት ይችላሉ።

እሱ እንደሚለው፤ ጀነሬተር ቢገዛ የሚሰራው በነዳጅ ስለሆነ የነዳጁ ጭስ በጤና ላይ ጉዳት እና የአካባቢ ብክለት የሚያስከትል ከመሆኑም በላይ ወጪውም ከፍተኛ እንደሆነ ካሰበ በኋላ ይህን ሁሉ ችግር የሚፈታ ጀነሬተር ለመስራት አቀደ። « በአነስተኛ ወጪ ምንም ጉዳት የማያደርስ የኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰጥ ጀነሬተር እንዴት ሰርቼ መብራት በሌለባቸው አካባቢዎች ላይ ተደራሽ ማድረግ እችላለሁ የሚለው ሀሳብ ቀን ከሌት ሳወጣና ሳወርድ ብዙ ጊዜ ፈጅቶብኛል» ሲል ያብራራል።

አምስተኛ ክፍል እያለ የጀመረውን ሀሳብ ከዳር ለማድረስ ሙከራ ሲያደርግ እስከ ሰባተኛ ክፍል ዘልቋል። በዚህ ሂደትም ሞባይል ቻርጅ ማድረግ የሚችል አምስት ዋት ኃይል የሚያመነጭ ጀነሬተር ሰራ።

ሰባተኛ ክፍል ላይ የተከታተለው የፊዚክስ ትምህርት ለፈጠራ ሥራው ተገቢ እውቀት እንዳስገኘለት ይናገራል። በዚህ የቴክኖሎጂ ዘመን በዓለም ያለኤሌክትሪክ ምንም አይነት ሥራ መስራት አይቻልም የሚለው ተማሪ አብዱራህማን፤ ቴክኖሎጂን ለመጠቀምና ለማስፋፋት፣ ለኢንዱስትሪም ሆነ ለሌሎች ሥራዎች የኤሌክትሪክ ኃይል ዋና ነገር መሆኑን ጠቅሶ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል የዓለም የጀርባ አጥንት መሆኑን ይጠቁማል።

ከውሃ፣ ከነዳጅና ከጸሀይ ኃይል የኤሌክትሪክ ኃይል አመንጭቶ ለሁሉም ተደራሽ ማድረግ የማይቻል በሆነበት ሁኔታ ምን አይነት ዜዴዎችን ተጠቀመን ይህን ወሳኝ የልማት አቅም ማመንጨት እንችላለን የሚለው ሀሳብ ሌላ አማራጭ በፈጠራ ሥራው እንዲያገኝ እንዳስቻለው ተማሪው ይናገራል።

በተለይ አካባቢ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የማይፈጥር፣ በቀላል መንገድና ወጭ የሚሰራና አገልግሎት የሚሰጥ ኃይል እንዴት ማመንጨት ይቻላል የሚለውን ለማወቅ አቅዶ የኃይል ማመንጫ ዘዴዎችን በሙሉ በማጥናት ወደ ሥራ እንደገባ ይናገራል። ለዚህም ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ አባይ ግድብና የመሳሳሉት ከውሃ የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያመነጨበትን መንገድ በማጤን እሱም ያለምንም የኤሌክትሪክ፣ የጸሀይ ወይም የነዳጅ ኃይል የኤሌክትሪክ ኃይል ማግኘት እንደቻለ ይገልጻል።

ተማሪ አብዱራህማን ጀነሬተር ከመስራቱ በፊት ለሁለት ዓመታት ጥረት አድርጓል። ስድስተኛ ክፍል የሳይንስ ትምህርት እንዲሁም በተለይ የሰባተኛ ክፍል የፊዚክስ ትምህርት የኤሌክትሮ ማግኔቲዝ ትምህርት መማሩ ሀሳቡን ለማዳበር እና ስለ ኃይል ማመንጨት በጥልቀት እንዲያጠና አስችለውታል። «ተጨማሪ እውቀት ፍለጋም በኦንላይን ላይ ያሉ ዶክመንተሪዎችንና የመሳሰሉትን ለሥራው የሚረዱኝን ጽሁፎችንና ቪዲዮዎችን በመመልከት መረዳት የምፈልገውን በደንብ መረዳት ችያለሁ። ይህም ሀሳቡን በደንብ ተረድቼ የፈጠራ ሥራውን ለመሥራት አስችሎኛል » ሲል አብራርቷል።

ሀይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይልን በመጠቀም ካለ ውሃ እንዴት ኃይል ማመንጨት ይቻላል ለሚለው መፍትሔ በማግኘት ባለ60 ዋት ኃይል ማመንጨት የሚችል ጀነሬተር መስራት ቻለ። ጀነሬተሩ ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀስም፣ የሁሉንም ሕብረተሰብ ክፍሎች

ተማሪ አብዱራህማን ከድር

ችግሮችንም እኩል መፍታት ይችላል። አስቸጋሪ በሚባሉ ቦታዎች ጭምር በሁሉም ቦታዎች በእኩል ጥቅም ላይ ሊውል የሚችልም ነው።

ለጀነሬተሮቹ «ከአብ ጀነሬተር» የሚል ስያሜ ሰጥቷቸዋል፤ ስያሜውን ከአባቱ ስም የመጀመሪያውን ፊደል እና ከራሱ ስም ደግሞ የመጀመሪያ ሁለት ፊደላት በመጠቀም እንዳወጣውም ይገልጻል።

ከተማሪ አቡዱራህማን የፈጠራ ውጤቶች መካካል የመጀመሪያው ሙከራ ያደረገበት 60 ዋት ኃይል ማመንጨት የሚችል ጀነሬተር ነው። ጀነሬተሩ የሚያመነጨው ትንሽ ኃይል ቢሆንም አንድ አምፑል፣ ቴሌቪዥን እና ስልክ ቻርጅ ያደርጋል።

ይህ የመጀመሪያ የፈጠራ ሥራው ለሁለተኛ ፈጠራ ሥራው መሠረት ሆኖ ሁለተኛውን 150 ዋት ኃይል ማመንጨት የሚችል ጀነሬተር መስራት አስችሎታል። «ባለ60 ዋቱ የመጀመሪያው ጀነሬተር የሚያመነጨው ትንሽ ኃይል ቢሆንም እጄን ያፍታታሁበት የመጀመሪያ ሥራዬ በመሆን ለፈጠራ ሥራ መሰረት ሆኖኛል፤ ቀጣዩን እንዲሰራ ብርታና ሞራል ሰጥቶኛል» ይላል።

ተማሪ አብዱራህማን እንደሚለው፤ ጀነሬተሮቹ በመብራት ኃይል የሚሰሩ ሁሉንም አይነት አገልግሎቶች መስጠት ያስችላሉ። የተገጠሙላቸው ቁሳቁስ እስካልተቃጠሉ ድረስ የሚሰጡት ኃይል ሳይቀንስና ሳይጨምር ያለምንም መቆራረጥ አገልግሎት መስጠት ይችላሉ። ቁሳቁሱ ቶሎ የማይቃጠሉና የማይበላሹ ቢሆኑም አጋጣሚ ሆኖ የሚቃጠሉና የሚበላሹም ከሆነ በቀላሉ ተቀይረው እንዲሰሩ ማድረግ ይቻላል።

ጀነሬተሮቹ ለአምፑል፣ ለቴሌቪዥን፣ ለስልክና ለመሳሳሉት በኤሌክትሪክ ኃይል ለሚሰሩ አገልግሎቶች የኤሌክትሪክ ኃይል በማቅረብ ይጠቅማሉ። መብራት በሌለባቸው አካባቢዎችና መብራት ለሚጠፋባቸው አካባቢዎች አገልግሎት መስጠትም ይችላሉ።

እሱ እንዳብራራው፤ ጀነሬተሮቹ በቀላል ወጪ የሚሰሩ ከመሆናቸው በተጨማሪ በአካባቢ ላይ ምንም አይነት ጉዳት አያስከትሉም። ጀነሬተር የመስራት ሀሳቡን ሲያመነጭ በቀላሉ ለመስራት የሚችልበትን ዘዴ ፍለጋ ላይ ትኩረት አድርጎ ሰርቷል። የመጀመሪያ ጀነሬተሩን የሰራው በ2014 ዓ.ም ነው፤ ከመጀመሪያው የፈጠራ ሥራ ያገኘው እውቀትና ልምድ ሁለተኛውን የፈጠራ ሥራ መስራቱን እንዳቀለለት ይገልጻል።

ሁለተኛው የፈጠራ ሥራውንም በ2016 ዓ.ም እንደሰራው አስታውሶ፣ ይህንን ለመስራትም አስራ አምስት ቀናት ብቻ እንደፈጀበት ይገልጻል። ሥራው ይህን ያህል የቀለለት ሊሰራው ያሰበውን ጀነሬተር አስቀድሞ በሀሳቡ አስቀምጦት ስለነበር ነው፤ በዚህም ስኬታማ በመሆኑ የሚፈልገው ከግብ ለማድረስ መቻሉን ያስረዳል።

እጁን ያፍታታበትና መነሻ የሆነው የመጀመሪያ የፈጠራ ሥራው እውቀትና ልምድ እንዲያገኝ ከማስቻሉ በላይ ብዙ እንዲያውቅና ሥራውን ይበልጥ በጥበብ እንዲሰራ እንደረዳው የሚናገረው ተማሪ አብዱራህማን፤ ሁለተኛው የፈጠራ ሥራው በአጭር ጊዜና በቀላሉ መስራቱ ከዚህ በመነጨ መሆኑን ይናገራል።

የመጀመሪያውን ጀነሬተር ለመስራት ብዙ ጊዜ እንደወሰደበት አስታውሶ፣ ጀነሬተሩን ለመስራት የሚያስፈልጉትን ቁሳቁስ በቅርበት ማግኘት ከተቻለ በቀላሉ መስራት እንደሚችል ይገልጻል። ጀኔሬተሮቹን ለመስራት የሚያስፈልጉትን ግብዓት በቀላሉ ማግኘት ከቻለ በአንድ ቀን ብዙ ጀነሬተር ማምረት እንደሚችልም ያስረዳል።

ተማሪው እንዳብራራው፤ እነዚህን ጀነሬተሮች ለመስራት ከሚያስፈልጉት ጥሬ ግብዓቶች አብዛኛዎቹ በሀገር ውስጥ የሚገኙ ናቸው። ለስራው ባትሪ፣ ዲኖሞ፣ የሙቀት መቆጣጣሪያ መሳሪያዎች እና የመሳሳሉት ያስፈልጋሉ። የመጀመሪያውን ባለ60 ዋት ጀነሬተር ለመስራት 135 ብር ብቻ ነው ወጪ የተደረገው ፤ ሁለተኛውን ባለ 150 ዋት ጀነሬተር ለመስራት ደግሞ ሁለት ሺ92 ብር ወጪ ተደርጓል።

ተማሪ አቡዱራህማን ሁለቱም የፈጠራ ሥራዎች ተፈትሸው አገልግሎት ላይ መዋላቸውን ጠቅሶ በተለይ የመብራት እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች ለሕብረተሰቡ ተደራሽ ሆነው አገልግሎት እየሰጡ እንደሚገኙ ይገልጻል። በፈጠራ ሥራዎች ከአእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት የባለቤትነት መብት ለማግኘት በሚያስችለው ሂደት ላይ መሆኑን አስታውቆ፣ በቅርብ የባለቤትነት መብት እንደሚያገኝ ይጠቁማል።

የፈጠራ ውጤቶች የመጀመሪያ ሙከራ ያደረገበት 60 ዋት ኃይል ማመንጨት የሚችል ጀነሬተር ለቤተሰቦቹ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን ይገልጻል። ሁለተኛው 150 ዋት ኃይል ማመንጨት የሚችል ጀነሬተርም እንዲሁ የኤሌክትሪክ ኃይል በሌለበት አካባቢ አርሲ ዞን ኮኮርሳ ወረዳ ጋጣ የምትባል አካባቢ ለሕብረተሰቡ አገልግሎት እየሰጠ ነው።

በዚህ አካባቢ ተደራሽ ሆኖ ለሕብረተሰቡ የመብራት አገልግሎቶች ለሚውሉ ለአምፑል፣ ለቴሌቪዥን ፣ የስልክ እና የመሳሳሉት እየሰጠ ይገኛል። « ጀነሬተሩን ለሰው ሰጥቼ ሕብረተሰቡ አገልግሎት እንዲያገኝ እያደረግኩ ነው። ለምሳሌ ስልክ በ20 ብር ሂሳብ ቻርድ የሚደረግ ሲሆን፤ አገልግሎቱን እየሰጠ ያለው ሰው አምስት ብሩን ለራሱ በመውሰድ፤ 15 ብር ገቢ ያደርግልኛል» ይላል።

ተማሪ አብዱራህማን በተለይ ሙከራ ተደርጎባቸው አገልግሎቱን እያገኙ ያሉ ሕብረተሰብ ክፍሎች የራሳቸው የሆነ ጀነሬተር እንዲኖራቸው በመፈለግ እንዲሰራላቸው እንደጠየቁት ይናገራል። ለእዚህም አንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች አብረው ገንዘብ በማጠራቀም በጋራ የሚፈልጉትን አይነት አቅም ያለው ጀነሬተር ሊሰራላቸው ማቀዱን ጠቁሟል።

በተጨማሪም ለአንድ ከተማ ነዋሪዎች እስከ 20ሚሊዮን ዋት ኃይል ማመንጨት የሚችል ጀነሬተር ለመስራት አቅዶ እየሰራ መሆኑን ይገልጻል። በአሁኑ ወቅት ደግሞ በአንድ አካባቢ ላይ ለሚኖሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል ባለ 1025 ዋት ጀነሬተር መስራት መጀመሩን ገልጾ፤ ጀነሬተሩን ለመስራት 750 ሺ ብር እንደሚያስፈልግ አስታውቋል። አሁን ላይ የጀነሬተሩን ንድፍ አስቀምጦ አስፈላጊ ሥራዎች እየሰራ መሆኑን አመላክተዋል።

ወደፊትም ከትምህርቱ ጎን ለጎን የፈጠራ ሥራዎች እየሰራና እያሳደገ እንደሚሄድ የሚገልጸው ተማሪ አብዱራህማን፤ «አሁን ላይ ዋንኛ ትኩረቴ ትምህርቴ ላይ ቢሆንም የጀመርኩትን ጀነሬተር እየሰራሁ ለሕብረተሰቡ ተደራሽ አደርጋለሁ። ሌሎች የሕብረተሰቡን ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉ የፈጠራ ሥራዎች ለመስራት አስባለሁ» ይላል።

የፈጠራ ሥራ ትኩረት ሰጥቶ ለመስራት ብዙ ጊዜና ብዙ ጥረትና ሙከራዎችን ማድረግን እንደሚጠይቅ የሚገልጸው ተማሪ አብዱራህማን፤ የፈጠራ ሥራ የመስራት ውስጣዊ ፍላጎት ካለ ውጣ ውረዱ ቢበዛም ከታሰበበት መድረስ እንደሚቻል ያመላክታል። እነዚህን የፈጠራ ሥራዎች ሲሰራ የቤተሰቦቹ ድጋፍና አስተያየት ከፍተኛ የሞራል ስንቅ እንደሆነው ጠቅሶ፣ ይህም ሥራዎቹን በትጋት እንዲሰራና ለውጤት እንዲበቃ እንደረዳው ይናገራል።

በተለይ ሀሳቡ ኖሯቸው የፈጠራ ሥራ ለመስራት የሚፈልጉ ተማሪ የፈጠራ ሥራ ባለሙያዎች የትምህርት ጊዜያቸውን በማይሻማ መልኩ ማስኬድ ይጠበቅባቸዋል። መማራቸው ለእዚህ ሥራቸው ወሳኝ መሰረት የሚጥልላቸውና እውቀት እንደሚጨምርላቸው አውቀው ከትምህርታቸው ጎን ለጎን ፈጠራዎች መስራት አለባቸው ሲል አስገንዝቧል።

ተማሪው፤ የፈጠራ ሥራዎቹን ሁሉም ሰው አውቋቸው ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ በኦንላይን ፣ በማኅበራዊ ሚዲያዎችና በአውደርዕይ ላይ በማቅረብ እያስተዋወቀ ይገኛል። ለሕብረተሰቡ የሚሰጡትን ጥቅም አይተው አውቀዋቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል ይጠቅማል ይላል።

እሱ እንዳለው፤ በቀጣይ የሰዎችን ፍላጎት መሰረት በማድረግ የተለያየ መጠን ያላቸው ጀነሬተሮች እያመረተ ሕብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ አቅዷል። ለኢንዱስትሪ፣ ለመኖሪያ ቤት እና በከተሞች የሚፈልጉ ሰዎች ካሉ በሚፈልጉበት ቦታ በሚፈልጉት ዋት መጠን እንደፍላጎታቸው እየሰራ ለማቅረብ ፍላጎቱ አለው።

በእዚህ መልኩ ወደ ማምረት ሲገባም ለሁለት ሺ ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር እንደሚችል ይገልጻል። ለአንድ ከተማም ይሁን ለፋብሪካ ትልልቅ ኃይል ማመንጨት የሚያስችሉ ጀነሬተሮችን የማምረት፣ ጀነሬተሮችን ሊቆጣጠሩ የሚችሉ ባለሙያዎችንም የማስልጠን እቅድ እንዳለውም አስታወቋል።

ፖለቲካና ወቅታዊ

ወቅታዊ ትንታኔ

የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ጉዞና ስኬቱ

አስቴር ኤልያስ

የዳበረ የዲፕሎማሲ ባሕል ያላት ኢትዮጵያ በለውጡ ዘመንም ይህንኑ በማስቀጠል ዘርፈ ብዙ ስኬት እያስመዘገበች እንደሆነ የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ። ኢትዮጵያ ቀደምት ከሚባሉና የረጅም ዘመን ዲፕሎማሲያዊ ታሪክ ካላቸው አገራት መካከል አንዷ ነች። በየዘመኑ የነበሯት መሪዎችም የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስጠበቅ የየበኩላቸውን ጥረት ማድረጋቸውንም የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ። በአሁኑ ወቅትም ኢትዮጵያ ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ አካሔድን በመከተል ሕዝቧን ከዲፕሎማሲ ፍሬ ተጠቃሚ በማድረግ ላይ ትገኛለች።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ኢትዮጵያ የተጓዘችበት የዲፕሎማሲ ሒደት ምን ይመስላል? ያስገኘውስ ውጤት እንዴት ይገለጻል? ስንል የዘርፉን ምሁራን ጠይቀናል፤ ምሁራኑ፣ ባለፉት አምስት ዓመታት ሲካሔድ የነበረው የዲፕሎማሲው ጥረት የዳበረውን የዲፕሎማሲ ባሕል ያስቀጠለ ሲሆን፣ በዚህም ዘርፈ ብዙ ውጤቶች የተመዘገቡበት እንደሆነ ያስረዳሉ።

ካነጋገርናቸው ምሁራን መካከል አንዱ በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በማኅበረሰብ ሳይንስ ትምህርት ቤት መምህር የሆኑ ዓለምሰገድ ደበሌ (ዶ/ር) ናቸው። የኢትዮጵን የመንግስት ግንኙነት ከአገራት ጋር ያለውን የዲፕሎማሲ ሒደቱን ስናይ አጠቃላይ ኢትዮጵያ የዳበረ የዲፕሎማሲ ባሕል ወይም ልምድ አላት ማለት እንችላለን ይላሉ። ያም ሆኖ ግን የኢትዮጵያ ዘመናዊ ዲፕሎማሲ የተጠናከረው በ20ኛ ክፍለ ዘመን አካባቢ ነው። በ20ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ ኢትዮጵያ የሊግ ኦፍ ኔሽን አባል መሆን የዲፕሎማሲ ውጤት እንደሆነም ያመለክታሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ በወቅቱ የጣሊያንን ወረራ አቤቱታን ለማቅረብም የተሞከረበት ነበር፤ እንደዚያ እያለ የቀድሞው አጠራሩ የአፍሪካ አንድነት/የአሁኑ አፍሪካ ኅብረት የተመሰረተው ኢትዮጵያ በተጫወተችው ዲፕሎማሲ ጥረት ነው። በኢትዮጵያ እንደየዘመኑ በነበሩት መሪዎች አተያይ የዲፕሎማሲውም አካሔድ ይለያያል።

በአጼ ኃይለስላሴ ዘመን የነበረው ዲፕሎማሲያዊ አካሔድ ከደርግ ዘመን፣ የደርግ ዘመኑ ደግሞ ከኢሕአዴግ ይለያያል። የመለየቱም ምስጢር ከርዕዮት ዓለም መቀየር ጋር ተያይዞ የሚተገበር በመሆኑ ነው። ስለዚህም ዲፕሎማሲው እየተከተለ የሚሔደው ያንን ነው።

ለምሳሌ በደርግ ዘመን መንግሥት ሲያጋድል የነበረው ወደራሽያ ነው፤ እንዲሁም የራሽያ አይነት ስልት ካላቸው አገሮች ጋር ዲፕሎማሲው ሲደረግ እንደነበር የሚታወስ ነው። በኢሕአዴግ ጊዜም እንደዚያው ግንኙነቱ ቀጥሎ ከእነ አሜሪካ ጋር እና ከሌሎች የአውሮፓ አገራት ጋር ግንኙነቱን ሲያደርግ ነበር ይላሉ።

የቀድሞው ዲፕሎማት ተሻለ ሰብሮ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ቀደም ሲል የነበረው የዲፕሎማሲ ሥራ ካስገኘው ስኬት ውስጥ አንዱ የቀድሞው አፍሪካ አንድነት ድርጅት የአሁኑ አፍሪካ ኅብረት መቀመጫውን አዲስ አበባ ሊያደርግ የቻለው በኢትዮጵያ ተጽዕኖ ፈጣሪነትና በተገኘው ዲፕሎማሲያዊ አካሔድ ነው ሲሉ ተሻለ (ዶ/ር)፣ የዓለምሰገድ (ዶ/ር)ን ሐሳብ ያጎለብታሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ እውነት ለመናገር በአንድ ወቅት በዲፕሎማሲው ረገድ ከፍታም፤ ዝቅታም ታይቷል። እንዲህም ሲባል ፈተናው ከበድ ያለበት ወቅት እንደነበር ለመጥቀስ ነው። ይህ አይነቱ ፈተና ደግሞ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በሌሎቹም አገሮች የሚያጋጥም ክስተት ነው። እንዲያም ሆኖ ትልቁ ስኬት ከዚያ ውስጥ በመውጣት ዛሬ ላይ መድረስ መቻል ሲሆን፣ ይህም የአሸናፊነት ምልክት ነው። በወቅቱ በኢትዮጵያ ላይ ተጠራርተውና ተደራርበው የመጡትን የጠላትን በትርና ምት በመቋቋም የተገኙት ውጤቶች ሊጠቀስ የሚችል ስኬት ነው።

ኢትዮጵያ እንደ አገር፣ እንደመንግሥትና ሕዝብ እንቅልፍ የላትም፤ ተግዳሮት ይበዛባታል። አንደኛ በዓባይ ግድብ ሲያጋጥመን የነበነረው ግብግብ ሲሆን፣ ይህ በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም። እሱ ሌላኛው የውጫሌ ውል ሆኖብን የሰነበተ ጉዳይ ነበር ይላሉ። የአውሮፓን ተጽዕኖ ተቋቁመው አገራችንን ከቅኝ ግዛት ነጻ ያደረገ ያ ትውልድ የሰራውን ያህል ተጋድልዎ በመስራት ግሩም በሆነ ዲፕሎማሲያዊ አካሔድ ከዓባይ ግድብ ጋር

ከቀይ ባሕር ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያ በኩል የቀረበው ጥያቄ በብዙዎች ዘንድ እውቅና እያገኘ የመምጣቱ ምስጢር የዲፕሎማሲ ሥራ ውጤት ነው

የነበረውን ፈተና አልፈነዋል ማለት ይቻላል። ጠንካራ የዲፕሎማሲ ሥራ በመሰራቱም ዛሬ የዓባይ ግድብ መጠናቀቅን ተከትሎ ሪቫን ሊቆረጥ ተቃርበልና፤ ይህ ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ስኬት ነው ሲሉ ያስረዳሉ።

ተሻለ (ዶ/ር)፣ አንዳንዶች ኢትዮጵያን ሁሌም አጣብቂኝ ውስጥ ለመክተት በብዙ ጥረት ይደረጋል፤ አንዱም በአገራችን የተካሔደው የሰሜኑ ጦርነት ነው ይላሉ። መንግስት ወደዚህ ጦርነት የገባው አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ ነው። ያለፈው የሁለት ዓመቱ ጦርነት በቀላሉ የሚታይ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ጥቂት የማይባሉ መንግስታትም በኢትዮጵያ ላይ ተጽዕኖ ለመፍጠር ጥረት ማድረጋቸው አይዘነጋም። ተግዳሮት ገጥሞን የነበረው በዲፕሎማሲያችን ድክመት ሳይሆን ተቀናቃኝ የሆነው አካል ዓለም አቀፍ ይዘት ባለው አካሔድ በመረባረቡ እንደሆኑ ዲፕሎማቱ ያመለክታሉ።

አክለውም ይህ የሰሜኑ ጦርነት ፈተና ግን በፈተናነቱ እንዳይዘልቅ በፕሪቶሪያ ስምምነት ጉዳዩ ተጠናቆ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ፈቷን ወደልማት መመለስ መቻሏ ሌላኛው ስኬት ነው። በሌላ በኩል ከግብጽ ጋር ያለው ግብግብ ምንም እንኳ እልህ አስጨራሽ የሆነ ቢሆንም ከመጋረጃ ጀርባ በተደረገው ዲፕሎማሲ ጥረትና ጥንቃቄ ኢትዮጵያ ውጤታማ መሆን እንደቻለችም ነው የሚናገሩት። ውጤቱን ሊያመጣ የቻለው የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ አመራርና የዲፕሎማሲ ብቃት ነውና መንግስታችንና ሕዝባችን የሚፈልገውን ነገር ማድረግ ችሏል። ይህ ቀላል ሥራ አይደለም ብለዋል።

ከለውጡ በኋላ እና በለውጡ ጊዜ ዲፕሎማሲው ቀጥሏል የሚሉት ዓለምሰገድ (ዶ/ር)፣ አንዳንድ አዳዲስና ለየት ያሉ እሳቤዎችም እየተጨመሩበት ያሉ መሆኑን ተናግረዋል። እንደ እርሳቸው አባባል፤ ለውጡ ከመጣ በኋላ ለየት የሚለው ዲፕሎማሲ የሚባለው ለምሳሌ ከአፍሪካ ቢጀመር ከአፍሪካ ቀንድ አገራት ጋር እርቅ ማውረድና ሰላም መፍጠር የሚል ነው። ለአብነት ያህል ለብዙ ዘመን ተቀያይመው የነበሩ የኢትዮጵያና_ኤርትራ ግንኙነት ከዓመታት በፊት ወደእርቅ መምጣትን ማስታወስ ይቻላል።

ሌላው የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ላይ ትኩረት ተደርጎበታል ያሉት መምህሩ፣ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ላይ ከአፍሪካ አገራት በተለይ ከምስራቅ አፍሪካ አገር እንዲሁም ከአፍሪካ ቀንድ አገራት በትብብር እንስራ የሚል አንድምታ ያለው ነው ብለዋል፤ ከአውሮፓ አገራት ጋርም እንዲሁ ግንኙነት እንደነበር ጠቅሰው፤ በእርግጥ ከአውሮፓ አገራት ጋር ያለን ግንኙነት አንዳንዴ ወጣ ገባ የሚል እንደሆነ አመልክተዋል። እንዲህ ለማለታቸው አንዱ ምክንያት በተለይ በሰሜኑ ጦርነት ጊዜ የነበረው የዲፕሎማሲያዊ አካሔድ በተለይ ብቅ ጥልቅ ማለቱን ተከትለው ነው። ነገር ግን ካለፈው ዓመት ጀምሮ ዲፕሎማሲው የተሻሻለበት ሁኔታ የታየበት ነው ብለዋል።

እንደ ዓለምሰገድ ገለጻ፤ በለውጡ ጊዜ እየታየ ያለው የዲፕሎማሲው ጥረት የዳበረውን የዲፕሎማሲ ባሕል የሚያሳይ ነው። ይህ ዲፕሎማሲ የሚጠቅመን ከአገራት ጋር መልካም ግንኙነት ለመፍጠር፣ የኢትዮጵያን ገጽታ ለማጎልበት፣ ኢንቨስትመንቶችን ለመሳብ፣ የንግድ ግንኙነቶችን ለማካሔድ፣ አገራዊ ፍላጎታችንን አስጠብቀን ለመጓዝ ነው። በአሁኑ ወቅትም እየተከናወነ ያለውም በዚሁ መልኩ ነው።

ልክ የሰሜኑ ጦርነት ኢትዮጵያ ባደረገችው ዲፕሎማሲያዊ አካሔድ በፕሪቶሪያው ስምምነት ውጤታማ ማድረግ እንደተቻለ ሁሉ፤ ብዙዎች የሚመኙት ግን ደግሞ ያልተሳካላቸውን የብሪክስ አባልነት ጉዳይ ኢትዮጵያ ልታሳካው መቻሏ በዲፕሎማሲው ረገድ ሌላኛው ትልቁ ስኬት እንደሆነ ገልጸዋል።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ስኬት የብሪክስ አባል መሆን ብቻ አይደለም፤ ከተለያዩ አገራት ጋር፣ ከአረብ ኢምሬቶች ጋር እንዲሁም ከቱርክም ጋር ጥሩ የሆነ የዲፕሎማሲ ግንኙነት ፈጥራለች። ወደ ሩቅ ምስራቅ ቻይና ስንሔድ ደግሞ እንዲሁ በፊት የተጀመረ የዲፕሎማሲ መሰረት እንደተጠበቀ ሆኖ እሱ ወደ ቋሚ ትብብር ያደገ መሆኑ የማይዘነጋ ነው። ቻይናውያን በኢትዮጵያ በብዙ ፕሮጀክቶች የሚሳተፉ ሲሆኑ፣ ሥራዎቻቸውንም በሰዓቱ በማጠናቀቅ የሚታወቁ መሆናቸው ያለውን መልካም ግንኙነት የሚያመላክት ነው። ኢንቨስትመንቶችን ወደ አገራችን በመሳብ በኩል ውጤት እንዳለም ጠቅሰው፤ ለአብነት ያህል የተባበሩት አረብ ኢምሬቶችም ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ትብብራቸውን እያጠናከሩ እንደሆነ ተናግረዋል።

ከሳምንታት በፊት በአንካራ የተደረገው የኢትዮጵያና የሶማሊያ ሁለትዮሽ ስምምነት በኢትዮጵያ ላይ ሊደረግ የታሰበውን ከበባ ያጨናገፈ ነው የሚሉት ደግሞ ተሻለ (ዶ/ር) ሲሆኑ፣ ይህ የዲፕሎማሲ ውጤት ነው ማለት ይቻላል ብለዋል። ከዚህም በላይ ሰላማዊ አየር መተንፈስ የሚያስችልም ነው ብዬ አስባለሁ በማለት አስረድተዋል። በእርግጥ እንዲህ ሲባል ብዙ ጥንቃቄዎች እንደሚያስፈልጉ ከግንዛቤ በማስገባት ነው፤ የማያስተኛ ፈተናም እንዳለ ሊታወቅ ይገባል። ምክንያቱም ሁኔታዎች ሲስተዋሉ ተኝተው የሚያሳድሩ አይነት አእንዳይደሉ ገልጸዋል።

እርሳቸው እንደሚሉት ከሆነ፤ እንዲያም ሆኖ ግን የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ጥርስ ያለው አንበሳ ነው ማለት ይቻላል። ኢትዮጵያ በአንበሳነቷ ትታወቃለች። እንዲህ ሲባል በባዶ መፎከርና ማቅራራት ሳይሆን በተግባር ተፈትኖ የተረጋገጠ በመሆኑ ነው። ለዚህ አንበሳነት ሌት ተቀን ለተጉ አካላትም ክብር ይገባቸዋል። ከዚህም በላይ መስራት ደግሞ ይቻላል። አገራዊ እድገታችንንና ለውጣችንን ብቻ ሳይሆን አሕጉራዊ ተሳትፏችንም ከዚህ በላይ ሊሆን እንደሚችል አምናለሁ። የትኛውንም ጉዳይ በአገር አቀፍ ደረጃ፣ በአፍሪካም ሆነ በዓለም አቀፍ መደረኮች ላይ በመግለጽም ሆነ በማሳመን ኢትዮጵያ ዛሬም ፈተኛው መስመር ላይ እንዳላች ብዙ ማሳያዎችን መጥቀስ ይቻላል። ስለዚህ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ከአገር አልፎ ለቀጣናውም ሆነ ለአህጉራችን የሚተርፍ መሆኑ እውን ነው።

ተሻለ (ዶ/ር) በጥቅሉ እንደሚናገሩት፤ ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው ረገድ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ስኬታማ ከሆነችባቸው አንዱ የዓባይ ግድብ ነው፤ ግድቡ ዛሬ ላይ መድረሱ ታላቅ የዲፕሎማሲ ውጤት ነው። የዲፕሎማሲ ውጤት ነው ሲባል በእርግጥ የአመራሩ፣ የሕዝቡም ጭምር መሆኑ ግልጽ ነው። ነገር ግን ግብጾች የዓባይ ግድብን በተመለከተ በጣም ብዙ ጊዜ በጽጥታው ምክር ቤት አጀንዳ ያስያዙበት ጉዳይ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ በኩል በድል ሊጠናቀቅ በመብቃቱ እጅግ የሚያስደንቅ ነው ማለት ይቻላል። ሁለተኛው የዲፕሎማሲ ድል ነው ብለው የሚገልጹት የሰሜኑ ጦርነት በሰላም መፍታት የተቻለበትን ሒደት ነው። ሶስተኛው የዲፕሎማሲ ድል ብዙዎች የሚፈልጉት ነገር ግን ያልተሳካላቸው የብሪክስ አባልነታችን ጉዳይ ነው። አራተኛው ደግሞ የግብጽንና መሰሎቿን ከበባ ለማፍረስ የተደረገው ሙከራ ሲሆን፣ ይኸውም የአንካራው ስምምነት ነው። አምስተኛው ደግሞ ከቀይ ባሕር ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያ በኩል የቀረበው ጥያቄ በብዙዎች ዘንድ እውቅና እያገኘ የመምጣቱ ምስጢር የዲፕሎማሲ ሥራ ውጤት ነው። ለአብነት ያህል በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያ ብቅ ብለው የነበሩ የፈረንሳይ ፕሬዚዳንት በዚህ ጉዳይ ለኢትዮጵያ የሰጡት ምላሽ መልካም የሚባል ነው።

ይህን የቀይ ባሕር ጉዳይ ኢትዮጵያ ባነሳችበት ወቅት ጎረቤት አገራትን ጨምሮ ሌሎች በምን ያህል ርቀት ጉዳዩን በአሉታዊ ጎኑ ሲያራግቡት እንደነበር የሚታወስ ነው። የጠቅላይ ሚኒስትራችን ርዕይ የሆነው የባሕር በር ጥያቄ በዓለም አቀፍ ደረጃ ብዙዎችን አሸብሮ እንደነበርም የሚታወቅ ነው። ነገር ግን ይህ ጉዳይ በተሰራው ዲፕሎማሲ እያደር ጋብ ብሎ ሲሞግቱን የነበሩ አካላት ሐሳባቸው እየተሸረሸረ የመጣበቱን ሁኔታ ማስተዋል ችለናል። በጥቅሉ ያለፉት አምስት ዓመታት የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲዊ አካሔድ ጠንካራና ውጤታማ ነው።

ልክ እንደ ተሻለ (ዶ/ር) ሁሉ ዓለምሰገድ (ዶ/ር)፣ ከሰሞኑ የፈረንሳይ ፕሬዚዳንት በጥቂት ዓመታት ውስጥ ሁለቴ ብቅ የማለታቸው ነገር የዲፕሎማሲ ጥረት ውጤት ነው ይላሉ። ፈረንሳውያንም እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት እያደረጉ የሚገኙ ናቸው። ከኢኮኖሚ ትብብር በተጨማሪ የባሕል ትስስሩን የማጠናከር ነገር ይታያል። ይህ ከበፊቱም ጀምሮ ያለ ሲሆን፣ ለምሳሌ ትምህርት ቤቶችን በማቋቋም፣ የጥናት ማዕከልንም በማቋቋም ረገድ ግንኙነታቸው የጎለበተ ነው ማለት ይቻላል። ዛሬም የሚታየው ነገር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቱ ሳይቋረጥ ቀጥሎ መሄዱን ነው ብለዋል።

ሌላው የአፍሪካ ኅብረት ኢትዮጵያ ውስጥ መቆየቱ በራሱ ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ አካሔድ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ምክንያቱም የአፍሪካ ኅብረት መቀመጫ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይሆን ከዚህ ቀደምም ቢሆን ብዙ ማንገራገር እንደነበር የሚታወቅ ነው። ዛሬ ያንን አስቀጥሎ መቆየቱ በራሱ አንድ ትልቅ ስኬት ነው ሊባል እንደሚችል ተናግረዋል።

የሰሜኑ ጦርነት ወደተኩስ አቁም መጥቶ ስምምነት ላይ እንዲደርስ እና መግባባት እንዲፈጠር መደረጉ ትልቅ ነገር ነው ሲሉ እንደ ተሻለ (ዶ/ር) ሁሉ ይናገራሉ። የፕሪቶሪያው ስምምነት የዲፕሎማሲ ውጤት እንደሆነም በመግለጽ የእርሳቸውን ሐሳብ ይጋራሉ። ብሪክስን መቀላቀልም እንደ አንድ አዲስ ነገር ማየት የሚቻል ሲሆን፣ ይህ ኢትዮጵያ ብሪክስን የመቀላቀል ጉዳይ የምዕራባውያንንና የአውሮፓውያንን ተጽዕኖ መቀነስ የሚያስችልም ጭምር ነው ይላሉ።

እንደ ዓለምሰገድ (ዶ/ር) ገለጻ፤ ኢትዮጵያ በቀጣናዊ ትስስር ረገድ ስትታይ በኢጋድ ያላት ሚና የሚጠቀስ ነው። በአብሮነት የመስራት መርሁም እንደ አንድ መልካም ነገር ሊታይ የሚችል ነው።

ምሁራኑ እንዳሉት ከሆነ፤ ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው ዘርፍ ውጤታማ ናት፤ በቀጣይ ብሔራዊ ጥቅማችንን አስጠብቀን ከጎረቤቶቻችን ጋርም ሆነ ከሌሎች ጋር የጀመርናቸውን ዲፕሎማሲያዊ አካሔዶች አጠናክሮ መሔድ ያስፈልጋል። ዲፕሎማሲያችንን ሊጎዱ የሚችሉ እንደ ሰላም መደፍረስ አይነት ችግሮቻችንን እየፈታን መሔድ ይጠበቅብናል። የውስጥ ችግሮችን ለመፍታት መጣሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ከውጭም በኩል ያለውንም መልካም ነገር አጠናክሮ ማስቀጠሉ ተገቢ ነው።

ለምሳሌ በዓለም አቀፍ ደረጃ ልንደመጥ በምንችልባቸው መድረኮች ሁሉ መስራትና በተለይ ከግብጽ ጋር ያለንን ሁኔታ እውነታውን ለማሳወቅ መጣር ያስፈልጋል። የተጀመሩ እንደተጠበቁ ሆነው ከአውሮፓ ኅብረት አገራት መሃል በእነሱም በመጠቀም የተሻለ የዲፕሎማሲ ውጤት እንዲገኝበት ማድረግ፤ በተለይ ኢንቨስትመንትን፣ ትብብርን፣ ኢኮኖሚ ፍሰትን እንዲሁም ንግድን የምናቀላጥፍበት ሁኔታ ቢመቻች መልካም ይሆናል።

በዚህ ዙሪያ ዲፕሎማቶቿ ንቁ ሆነው በአገሪቷ አንገብጋቢ ጉዳዮች ላይ መሳተፍና ዲፕሎማሲውን ማቀላጠፍ ይጠበቅባቸዋል። ድሮ እንደሚደረገው ወደ አንድ አገር ከሔዱ በኋላ ጎን ለጎን የግል ሥራ መሥራትና ሌላ ሌላ ነገር ማድረግ ሳይሆን ዘመኑን የዋጀ ዲፕሎማሲያዊ አካሔድን በመከተል ለአገር የሚተርፍ የዲፕሎማሲ ሥራ መስራት ይኖርባቸዋል።

ማህበራዊ

ሴቶች

ወጣት ሴቶችን ለማብቃት የወጣት ማርታ ሕልም

አመሰወርቅ ከበደ

ሌሎችን የምትረዳበትን መንገድ መፍጠር የልጅነት ሕልሟ ነው። ይህ ፍላጎቷ ጠንካራ ከመሆኑ የተነሳ ገና በአፍላ እድሜዋ ነበር ከጓደኞቿ ጋር በመሆን መጽሐፍት የማግኘት እድል የሌላቸውን ተማሪዎች ለመርዳት አነስተኛ ቤተ መጻሕፍት ለመክፈት ያስቻላት።

መጻሕፍት ባነበቡት፣ ፊልም ባየች ቁጥር ሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጫና ስትመለከት ሴቶችን መርዳት የምንግዜም ምኞቷ ነበር። እናም ይህ ምኞቷ ፍላጎት ብቻ ሆኖ አልቀረም፤ ዛሬ ላይ በውስጧ የበቀለው ሴቶችን የመርዳት ዓላማ አድጎ፤ ወጣት ሴቶች ላይ የሚሰራ በጎ አድራጎት ድርጅት እስከማቋቋም ደርሳለች።

በዛሬው የሴቶች ዓምድ እትማችን የሀገር አቀፍ ወጣት ሴቶች በጎ አድራጎት ድርጅት መስራች እና አስተዳዳሪ የሆነችውን ወጣት ማርታ ማሙዬን ተሞክሮ እናካፍላለን።

ወጣት ማርታ አዲስ አበባ ከተማ አራት ኪሎ አካባቢ ተወልዳ ያደገች ሲሆን፤ ሁሉንም የትምህርት ደረጃዎችን ያጠናቀቀችው እዚሁ ከተማ ነው። የመጀመሪያ ዲግሪዋን በኮምፒውተር ሳይንስ ከተማረች በኋላ፤ ሁለተኛ ዲግሪዋን ደግሞ በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን ለማጠናቀቅ ችላለች።

"በልጅነቴ መጻሕፍትን ሳነብ፣ ፊልሞችን ስመለከት በሴቶች ላይ የሚደርሱ ነገሮች ያሙኛል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የነበረኝ ቁጭት እያደገ መጥቶ ነው መሰለኝ ሁልጊዜ የማስበው በሴቶች ላይ መስራት ነው። ሴቶችን የሚያግዝ በብቃት፣ በሥራ ፣ በዓላማ ጠንክረው እንዲወጡ የሚያግዝ ትልቅ ሥራ መስራት እመኝ ነበር "ትላለች።

በልጅነቷ አራት ኪሎ አካባቢ ቤተ መጻሕፍት እንዳ ቋቋመች ትናገራለች ፤ ለዚህ ደግሞ ያነሳሳት፤" ሰባተኛ እና ስምንተኛ ክፍል እየተማርን ቤተመጻሕፍት ስንሄድ ስለሚሞላብን መጻሕፍ ተከራይተን ነበር የምናነበው። መጻሕፍ ለመከራየት ከሆነ ቤተሰብ ገንዘብ ለመስጠት ስለማይጨክን ለምነንም ቢሆን ተቀብለን እንከራያለን። ነገር ግን ተከራይቶ ለማንበብ አቅሙ የማይፈቅድለት ተማሪ አለ። " ስትል ትናገራለች።

እናም ማርታ እነዚህ ከፍለው መጻሕፍ መከራይትና ማንበብ የማችሉ ተማሪዎች ነገር ስለሚያሳስባት፤ ሁሌ ሰፊ ቤተመጻሕፍ ቢኖር እያለች ትመኝ የነበረው። ምኞቷ ወደ እውነታው ተቀየረና ስምንተኛ ክፍል ስትደርስ ከጓደኞቿ ጋር በመሆን ቤተ መጻሕፍት ለማቋቋም ቦቃች።

ተከራይተው ማንበብ የማይችሉ ተማሪዎችን ለመርዳት ቤተመጻሕፍት ማቋቋም እንደምትፈልግ ነገረቻቸው ። በወቅቱ እንዲያነቡ የተፈቀደላቸው ቤተ መጻሕፍ ነበር እና ሌሎች ተማሪ ጓደኞቻቸው ማንበብ እንዲችሉ አስፈላጊ የሆኑ መጻሕፍትን በማሟላት ወደተሟላ ቤተ መጻሕፍትነት ቀየሩት።

"በቤተ መጻሕፍቱ እኛም እናነባለን ሌሎች ተማሪዎችም ገብተው መጠቀም ስለጀመሩ እየሰፋ መጣ። ቤተመጻሕፍቱ እየሞላ ተከራይተን ወይም ውጪ ድንጋይ ላይ እየተቀመጥን በማንበብ መቸገራችንን በማየት፤ ከትምህርት ቤት ውጭ አንድ የወጣቶች ቤተመጽሓፍት ነበረና እዛ እንድናነብ ተፈቀደልን። "ትላለች።

"በቤተመጽሀፉ የትምህርት መጻሕፍትን ጨምሮ የተለያዩ ልቦ ወለዶች እና ታሪካዊ መጻሕፍቶች ነበሩ። ከዛን ወደ ሰብሳቢው በመሄድ ዝም ብለው የተቀመጡ መጻሕፍት ይሸጡና፤ እኛ ለትምህርታችን የሚያዘጋጀንን ወቅታዊ መጻሕፍት እናምጣ ብለን አማከርነው። "በማለት ትገልጻለች።

በዚህ ሁኔታ በቤተመጻሕፍቱ የተለያዩ መጽሓፍ እንዲሟላ አደረጉና ሌሎች ተማሪዎች ለትምህርታቸው የሚጠቅማቸው መጻሕፍት እንዲያገኙ መንገድ ከፋች ለመሆን በቁ። ቤተ መጻሕፍቱን ለሌሎች ተማሪዎች በሚሆን መልኩ የማደራጀቱ ሀሳብ መጀመሪያ ላይ የማርታ ቢሆንም፤ ከዛ በኋላ ስትሰራ የነበረው ምኒልክ፣ መድኃኒያለም እና ናዝሬት ትምህርት ቤት ከሚማሩ ጓደኞቿ ጋር ነበር። እነ ማርታ በቤተ መጻሕፍቱ

> "ትምህርት እና ኪነ ጥበብ እያልኩ ባድግም፤ ሁሌም የሴቶች ነገር ውስጤን ይነካዋል:: ከራሴ ጋር አነጻጽራለሁ፤ እኔ መሃል ከተማ አራት ኪሎ ተወልጄ ሴቶች ላይ የሚደርሱ አንዳንድ ተጽዕኖዎችን ስመለከት፤ ሌሎች አካባቢዎችስ እንዴት ሊሆን ይችላል የሚለው ያሳስበኛል::"

እስከ አስረኛ ክፍል ድረስ ከሰሩ በኋላ ለተቋሙ አስረክበው። አሁን ላይ ያ ቤተ መጻሕፍቱ መፍረሱን ትናገራለች።

ማርታ ሌሎችን ለመርዳት ካላት ፍላጎት ባለፈ ኪነጥበባዊ እና ስፖርታዊ ነገሮች በጣም ስለሚስባት በእንደዚህ አይነት መርኃ ግብሮች ላይ ትሳተፍ ነበር። አፍላ እድሜ ላይ እያለች በሞዴሊንግ እና ኪነጥበባዊ ጉዳዮች ላይ ከመሳተፍ በተጨማሪ ማርሻል አርት ላይ ለአምስት ዓመት ተሳትፋለች።

"ትምህርት እና ኪነ ጥበብ እያልኩ ባድግም፤ ሁሌም የሴቶች ነገር ውስጤን ይነካዋል። ከራሴ ጋር አነጻጽራለሁ፤ እኔ መሃል ከተማ አራት ኪሎ ተወልጄ ሴቶች ላይ የሚደርሱ አንዳንድ ተጽዕኖዎችን ስመለከት፤ ሌሎች አካባቢዎችስ እንዴት ሊሆን ይችላል የሚለው ያሳስበኛል። "ትላለች።

እነዚህ ነገሮች ስታስብ ሴት ወጣቶች ላይ ብዙ ነገር ለመስራት ሀሳብ አደረባት። በትምህርት እና ስልጠና ግንዛቤዋ እያደገ ሲመጣ የራሷን በጎ አድራጎት ድርጅት ከመክፈቷ በፊት በተለያዩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ በመሳተፍ የምታገለገል ሲሆን፤ ከእነዚህ ተቋማት

ማርታ ማሙዬ

ጋር ስትሰራ ፕሮፖዛሎችንም ታዘጋጅ ነበር።

"የአመራርነት እና ሌሎች የተለያዩ አይነት ስልጠናዎች በየግዜው ስወስድ አቅሜን እያዳበርኩ መጣው። ዲግሪዬን ስማር በኢትዮጵያ ወጣቶች ፌዴሬሽን እሳተፍ ስለነበር አመራር ሆኜ ተመረጥኩ። "ስትል ትናገራለች።

በፌዴሬሽኑ አመራር ሆና ስትመረጥ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሴት ወጣት አመራሮች እና ሙያተኞች የሚል ዘርፍ እንዲቋቋም አደረገች። በዚህም በየክልሉ በርካታ ወጣቶችን በማግኘት የግንዛቤ ሥራ ለመስራት ቻሉ ። ከዛን እሷ የዘርፉ ሰብሳቢ እንድትሆን ተደረገ።

ማርታ በፌደሬሽኑ ስትመራው የነበረችውን ዘርፍ፤ እንደ መደበኛ ድርጅት ለመክፈት ሀሳብ አደረባት። ከሶስት ዓመት በፊት የመጀመሪያ ዲግሪዋን ካጠናቀቀች ከአንድ ወር በኋላ፤ አሁን የምትመራውን ሀገር አቀፍ ወጣት ሴቶች በጎ አድራጎት ድርጅት ለማቋቋም ሂደቱን ጀመረች።

"እራሱን የቻለ ድርጅት ለማድረግ ስለፈለኩ አማከርኳቸው እና ተመዝግበን፤ በቦርድ እንዲመራ በማድረግ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ተመሰረተ። ለቀጣይም ትልቅ ዓላማ ነው ያለን።" ስትል ታስረዳለች።

"ድርጅቱን የመጀመር ድፍረቱ የመጣው ሴቶች ላይ የሚያጋጥመውን ችግር ባየው ቁጥር ደፋር እንድሆን አደረገኝ። እዚህ ቦታ ላይ ተቀምጬ ምን አለ ትንሽ ነገር ማድረግ ብችል የሚለው ሀሳብ ደግሞ ውስጤን ይገፋዋል። አብረውኝ ያሉ ሰዎች ሀሳቤን ሲቀበሉ ሲደግፉኝ እና አንዳንድ እድሎች ሳገኝ እየተጠቀምኩ፤ ድርጅቱን ወደ መሬት አወረድኩ።" ትላለች።

ማርታ ትምህርቷን ካጠናቀቀች በኋላ ተምሬያለሁ፣ ልምድ አለኝ በማለት ተማሪ እያለች ትሰራቸው የነበሩ ሥራዎችን መበተን ከቦዳት። ስለዚህ እንደ ሀገር አሁን የምትሰራውን ሥራ እየሰራች፤ በቀጣይ ደግሞ ሌላ አቅም ለማዳበር ወስና ወደ ሥራው ገባች። ይህም ውስጣዊ እርካታ እንደሰጣት ትናገራለች።

የድርጅቱ መስራችና ሥራ አስኪያጅ ብትሆንም፤ የደረሰባቸውን ነገር ለማማከር ስለምትቀላቸው የተለያዩ ወጣት ሴቶች ወደ ማርታ በመምጣት በግልጽ ችግራቸውን ይገልጹላታል ። መፍትሄ መስጠቱ በድርጅቱ አቅም የሚቻል ከሆነ እንዲረዱ የሚደረግ ሲሆን፤ ከእዛ ከፍ ያለ ከሆነ ደግሞ አቅም ካላቸው አካላት ጋር በአፋጣኝ እንዲደርስ ይደረጋል።

"ድርጅቱ በቦርድ የሚመራ እና የራሱ የገንዘብ ስርዓት ያለው ሲሆን፤ ከአንድ አንድ ለጋሾች ከሚገኙ ድጋፎች ባለፈ፤ ፈንድ የማግኘት ነገር በጣም ትንቅነቅ ነው። በተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተወዳድረን ድርጅታችን ሲያልፍ የምናገኛትን ፈንድ ያለንን ልምድ እና ግንኙነቶች በመጠቀም በትንሽ ብር በዙ ነገር እንሰራለን።" ትላለች።

ድርጅቱ የተቋቋመበትን ዓላማ የምትገልጸው ማርታ፤ "ትልቁ ዓላማው ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ሙብት ላይ በቴክኖሎጂ በመታገዝ ሴት ወጣቶችን ማብቃት ነው። ልክ እንደ ዓላማው አሁን ድርጅቱ እየሰራ ያለው መሰረታዊ በሆነ መልኩ የሴት ወጣቶችን ሕይወት መቀየር ነው። "ስትል ትገልጻለች።

ለአብነትም ከሁለት ዓመት በፊት ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ እና ከዩኒቨርሲቲ ውጭ ከሰባት የመንግስት አካላት ጋር በመፈራረም፤ በአደንዛዥ እጽና በሌሎች ወጣቶች ላይ ተጽዕኖ በሚያደርሱ ችግሮች ዙሪያ ለስምንት ወራት በመስራት ከ ስድስት ሺህ 500 በላይ ሰዎች ጋር መድረሳቸውን ታስረዳለች።

"ስልጠናው የተሰጠው በአካባቢው ለሁሉም ማኅበረሰብ ነበር፤ ምክንያቱም ወጣቱ የሚኖረው በማኅበረሰቡ ውስጥ ስለሆነ ከሱስና ከሌሎች እኩይ ተግባራት ጋር ተያይዞ ግንዛቤው ለሁሉም የማኅበረሰብ ክፍል ያስፈልገዋል። ለዚህም የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መንገዶችን አድርገናል።" ስትል ትገልጻለች።

ሌላው በአራዳ ክፍለ ከተማ 15 ድርጅቶች በኮቪድ ምክንያት የተበላሸባቸውን ከአከሽን ኤይድ ጋር በመተባበር ድጋፍ እንዲደረግላቸው አድርገዋል። ድርጅቱ እነዚህን ድጋፎች ሲያደርጉ በትናንሽ ገንዘብ ለመፈጸም ጥረት ያደርጋል።

በትንሽ ገንዘብ በርካታ ሥራዎችን እንዴት እንደሚያከናውኑ የምትናገረው ማርታ፤ "የመጀመሪያው በማኅበረሰቡ የሚሰሩ ሥራዎችን የራሱ አድርጎ እንዲወስድ ማድረግ ሲሆን፤ ሌላው በሰው ኃይል ረገድ እንደ አስፈላጊነቱ ሰው ይቀጠራል። እንዲሁም ብቃቱ ያላቸውን በጎ አድራጊዎች በመጠቀም ሥራዎች እንዲሰሩ ይደረጋል።፣" ትላለች። በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ 175 ወጣቶችን በመለየት ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመሆን የወጣቶቹን አቅም በሚያሳድጉ ሥራዎች እየተሰሩ ነው ።

"ድርጅቱ ወጣት ሴቶችን ዓላማ አድርጎ የተመሰረተ ቢሆንም፤ ወጣት ሴቶችን የሚደግፉ ሥራዎች በሚሰሩበት ወቅት፤ ወጣት ወንዶችንም ማካተት አስፈላጊ ስለሚሆን እነሱንም ተደራሽ እናደርጋለን። ነገር ግን ሴቶች ያላገኙት እድል አለ ብለን ስለምናስብ የምንሰራውን ሥራ ሁሉ በሴቶች ላይ እናጎላለን። "ስትል ታስረዳለች።

"ከሴቶች ጥቃት ጋር ተያይዞ ሥራዎችን ስንሰራ የኢጋር ድርጅቶችን ጥናት ለመመልከት እንሞክራለን። በዚህም በስፋት የሴቶች ጥቃት በገጠሪቱ የሀገሪቱ ክፍል ብቻ እንዳለ ነው የሚታሰበው። ነገር ግን ከተማ ላይ ከፍተኛ የሆነ የሴቶች ጥቃት ነው ያለው።" ትላለች። "ከተማ አካባቢ አውቃለሁ በሚል ቀለል ተደርገው የሚታዩ መንገዶች በራሱ ለጥቃት ሰለባ እያደረጉ ነው። የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀማችን በአራሱ በቀላሉ ለጥቃት እንድንጋለጥ ያደርጋል። ስልጣኔ እየመሰሉ ወጣቱን ይዘው የሚጠፉ በርካታ ችግሮች አሉ ፤ ይሄ በራሱ ጥቃቱን ያሰፋዋል። "ስትል ታስረዳለች።

"ከሕግ አፈጻጸም ጋር ተያይዞ ያሉ ክፍተቶችም ጥቃትን እንዲሰፋ ያደርጋሉ። በኢትዮጵያ ጥቃትን በተመለከተ የተለያዩ ሕጎች አሉ። እነዚህ ሕጎች በአግባቡ ተፈጻሚ ቢሆኑ መልካም ነው። ለምሳሌ እንደ ሀገር ጥቃት ያደረሰው አካል እያለ፤ ተጎጂው አካል ነው የሚሸማቀቀው። ሌሎች ሀገራት ላይ ግን ጥቃት ፈጻሚው ከማኅበራዊ ሕይወቱ ሳይቀር ሊገለል ይችላል ። በጥቃት አድራሾች ላይ የሚሰጠው ብያኔ ከጥቃቱ አንጻር አናሳ ሆኖ የሚታይበት ሁኔታ አለ። ይሄ ደግሞ ጥቃቱ እንዲሰፋ አድርጎታል "ትላለች።

አሁንም ቢሆን ሥራችንን ጀመርን እንጂ አልጨረስንም የምትለው ወጣት ማርታ፤ ብዙ ሊሰራባቸው የሚገቡ፣ ትኩረትን የሚሹ ችግሮች አሉ። በእነዚህ ረገድ ከኢጋር አካላት ጋር በመሆን በርካታ ሥራዎች በመስራት ውጤታማ እና ተሳታፊ ወጣቶችን የማብቃት እቅድ እንዳለ ትናገራለች።

ሴቶች ሁሌም አንገታቸውን ደፍተው እንዳይኖሩ ራሳቸውን በትምህርት ማሳደግ አለባቸው። በግል ጥረት የሚመጣ እውቀት ከፍተትን ስለሚሞላ በሁሉም አቅጣጫ ሙሉ ለመሆን ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። በእውቀት ላይ የታገዘ የኢኮኖሚ አቅምን መገንባት ደግሞ ወሳኝ መሆኑን ትመክራለች።

ማረፊያ

አዲስ ዘመን ድሮ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

ትናንትን በዛሬ፣ ከአዲስ ዘመን ዘመን አይሽሬ የትውስታ መንገዶች ላይ ካገኘናቸው መካከል “የዳቦ ነጋዴዎቹ እየቆመሩብን ነው” ለመሆኑ ምን ይቆምራሉ... ያደባባዩ አማጭ ደግሞ በጆሮ ከቀዳው ለአንባቢያኑ ያካፍላል። ጥቂት ከዓለም ወሬዎችም ከሚባለው እንካፈልና በዛሬ እይታ ውስጥ ፈገግታን ሊያጭሩብን ከሚችሉት ከጥንቱ ማስታወቂያዎች እንተዋወቅ።

የዳቦ ነጋዴዎች እየቆመሩብን ነው

ዳቦ-ድሮ ቀረ ከሚባሉ ነገሮች አንዱ ነው። ዳቦ መጠኑ በሚያሳዝን ሁኔታ እየቀነሰ ጥራቱም እያሽቆለቆለ፣ ዋጋው ደግሞ እየተተኮሰ ይታያል።

...

የድሮ ዳቦ ዳቦ መልኩ ብቻ ይበቃ ነበር ብል የምን ማጋነን ነው እንደማትሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ።

...

ወዝ የሌለው ዳቦ በየቦታው ሞልቷል። ዳቦ ከተባለ ማለቴ ነው። እንቡጥ አይገኝበትም። ያሳስራል፣ ያስቀጣል፣ ተበለው ይሆን ውሃ አጥቶ እንደደረቀ ቅጠል የሚያቆረፍዱት፤ በእዚህ ላይ መጠኑ በጣም እጅግ ያስገርማል። ኪኒን እያከለ መጥቷል። በእዚህ ላይ ተፈርፍሮ የሚያልቀውና ቤት የሚያበላሸው አይነሳም። የሀምሳ ሳንቲም ዳቦ ስትገዛ የሁለት ብር መጥረጊያ መግዛትህን እንዳትረሳ እየተባለ የሚነገረውም ለዚሁ አይደል፤ የሱሙኒ ዶሮ የብር ገመድ ይዛ ጠፋች አይነት መሆኑ ነው።

...

ዛሬ ሕጻናት ሁለት ዳቦ በልተው አይጠግቡም። እረ ይጨመርልን በሚል እያጉተመተሙ ነው ወደ ትምህርት ቤት የሚጓዙት። ገና አንድ ክፍለ ጊዜ ሳይጨርሱ ሆዳቸው ምግብ ይጠይቃቸዋል። አዋቂዎች አፋቸው ባዶ ባዶ እንዳይል ካልሆነ በስተቀር የዘመኑ ዳቦ አላረካቸውም። ግማሹ ለአፈር የተቀረው ለከንፈር በመሆኑ ከሆድ አይደርስም።

...የምንበላው ሳይሆን የምንስመው ዳቦ መጥቷል። የዳቦ ነጋዴዎች እስከመቼ ነው የሚቆምሩብን፤ ነዳጅ ጨመረ ሲባል በዚያው ልክ ዋጋ ይጨምሩብናል። በ20 ሳንቲም ይሸጥ የነበረው ዛሬ እየቀረ ነው። አንዳንዶቹ የ20 ሳንቲሙን 50 ይቀበሉበታል። ግፍ የፈሩ ደግሞ የ50 ሳንቲሙን 60 ይቀበሉበታል።

...

የዳቦ ነጋዴዎች በእኛ ስቃይ እንዴት ይከብራሉ፤ ባንገዛቸውስ፣ ሌላ መላ መፈለግ አቅቶን ነው፣ እንደኔ እምነት ግን በአንድ ሰሞን ዘመቻ ዳቦ ቤቶችን ልክ ማግባት የሚቻል ይመስለኛል። ዘንድሮስ እየቆመሩብን አይኖሩም የእስካሁኑ ይበቃል ባዮች በዝተዋል። እባካችሁ ጉዳዩ የሚመለከታችሁ ሁሉ የዳቦ ቤቶችን አሠራር የሚያስተካክል አፋጣኝ እርምጃ ውሰዱ።

(አዲስ ዘመን መጋቢት 24 ቀን 1984ዓ.ም)

ከዓለም ዙሪያ የተገኙ ወሬዎች

ከዮሐንስበርግ፤ (ደቡብ አፍሪካ) በኤልሳቤጥ ቤል ከተማ ውስጥ በታወቀው (ቆኢሊር) በተባለው የቴአትር አዳራሽ ውስጥ በሚታየው የሼክስፒር ቴአትር ውስጥ ገብተው ለመመልከት አንድ ጠይምነት ያለው መምህርና 4 ተማሪዎቹ ገንዘባቸውን ከፍለው የመግቢያ ወረቀታቸውንም ካስቆረጡ በኋላ በመልካቸው ያለመገርጣት ምክንያት ተከልክለው ገንዘብ በሚከፈልበት በር ላይ ተገፍትረው ወጥተዋል። ገንዘቡም አልተመለሰላቸውም።

(አዲስ ዘመን ግንቦት 8 ቀን 1952ዓ.ም)

ከሞስኮው “ሰማይ ለሁሉም ክፍት ነው” ሲል የአሜሪካ መንግሥት ያቀረበውን አሳብና ለራሱ ሚስጢር ፍለጋ የሚጠቀምበትን ጉዳይ አንስተው የሞስኮብ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሚስተር ግሮሚኮ ሲያመለክቱ “ይኸንን የሞስኮብ መንግሥት ይቀበለዋል ማለት ዘበት ነው” ካሉ በኋላ የሞስኮብ መንግሥት ሰማይ ዝግ ነው። ለወደፊቱም ቢሆን ዝግ እንደሆነ የሚኖር ነው” ብለው ለቀረበላቸው ጥያቄ መለሱ።

(አዲስ ዘመን ግንቦት 8 ቀን 1952ዓ.ም)

ያደባባዩ አማጭ

መቼም ያየሁትንና የሰማሁትን አልደብቅም እናገራለሁ ብያለሁና አሁንም እንደ አፍዛዥ ሆኖ የሰማሁትን ላውራላችሁ።

ግንቦት 1 ቀን 1952ዓ.ም ያንኑ ሰብሳቢውን አውቶብስ ለመጠበቅ(ለመሳፈር) ከኪንግ ጆርጅ ቡና ቤት በስተ ጎን ካለው የአንበሳ መቆሚያ ቆሜ የፓሪስን ውዝግብ ጋዜጣ ሳነብ በአጠገቤ አንዲት ድንቡልቡል፣ ሽቅርቅር ብላ በሀገር ልብስ አጊጣ አድራሽ አጥታ እንደኔው አውቶብስ ስትጠብቅ አንዱ ለፍቶ፣ ደክሞ አዳሪ ቀረብ ብሎ “እንደምን አድረሻልና መቼ እንገናኛለን? ብሎሻል ጋሼ” አላት። እርሷም “ደኅንነቱንስ ያው ነኝ፤ ኸረ ለመሆኑ እርሱ ከኔ የሚፈልገው ምንድር ነውና ይህን ያህል አንተን ያመላልስሃል? ምን እንዳደርግለት ይፈልጋል? አንተስ ጉዳዩን ገልጸህ ለምን አትነግረኝም?” አለችው። ያም አማጭ ከአንቺ የሚፈልገው እሺታሺን ነው። ዓላማውም ለትዳር ነውና እሺ በይው ምንም እንኳን አንቺ በመምህርነትሽ የኔንና የርሱን ሁኔታ ብታርሚና የወር አበልሽም በርከት ያለ ቢሆን እርሱም...ነውና የተፈላለጋችሁበት ጉዳይ የተሳካ ይሆናል አለና የአማጭነቱን ያህል አስረዳ።

ወይዘሪትም (ግን እንጃ) እስቲ ሁሉንም ነገር አብራርቶ በቁጥር...በስልክ ደውልልኝና በሰፊው እንነጋገርበታለን። እኔና አንተ ብቻ እዚህ ልንጨርሰው አልበቃንም፤ እንዳይረሳ አስጠንቅቀውና ስልክ እንዲደውልልኝ” ብላው አውቶብሱ ላይ ቁጢጥ አለች። እኔ እዚህ ላይ ስለሁለት ነገሮች ብቻ አዝናለሁ።

1ኛ/ ጋብቻን ያህል ነገር አጀማመሩ በእንደዚህ ያለ ሁኔታ በመሆኑ ፍጻሜው አያምርም ያው ነው።

2ኛ/ በቀደም እንዳወራኋችሁ ሁሉ የመንግሥቱ ስልክ እንደዚህ ለመሰለው የእንቆቅልሽ ጨዋታ እንደፈረደበት ተተኝቶበት መዋሉ ነው። የሆነ ሆኖ ፒያሣ ላይ ከተጫጨ ተድረው ፒያሣ ላይ ለመታየት ያብቃቸው። ግን ሁለቱ ፒያሣ ተጠፋፍተው እንዳይቀሩ ያድርጋቸው።

ማሞ ውድነህ(ዋግ ድሃና)

(አዲስ ዘመን ግንቦት 8 ቀን 1952ዓ.ም)

ማስታወቂያ

ፊልም በሚታይበት ጊዜና ፊልም ለመለወጥ ብርሃን በሚደረግበት ጊዜ የብልግና ድምጽ ምልክት የሚሆን ፉጨት ድምጽ ሰሚዎችን እስከማደንቆር ይሰማል። ይህ ከጠላት የተወረሰ የብልግና ድምጽ እንዳይሰማ እያስጠነቀቅን፤ የፉጨት ድምጽ የሚያሰሙትን የሚያስገድዱ ፖሊሶች መታዘዛቸውን እናስታውቃለን።

(አዲስ ዘመን መስከረም 8 ቀን 1941ዓ.ም)

ጥቅምት 18 ቀን ሐሙስ ጧት ባለ ቀንድ መያዣ የዓይን መነጽር ዑራኤል ስለጠፋብኝ፤ አግኝቶ ጋዜጣና ማስታወቂያ መሥሪያ ቤት ድረስ ላመጣልኝ ወሮታውን እከፍላለሁ።

(አዲስ ዘመን ጥቅምት 20 ቀን 1951ዓ.ም)

ዓለም አቀፍ

አስከፊ አደጋ የደረሰባት ደቡብ ኮሪያ በቦይንግ አውሮፕላኖች ላይ ፋተሻ እንዲደረግ አዘዘች

18ነ ሰዎችን አሳፍሮ ሲጓዝ የነበረው አውሮፕላን በማረፊያው ላይ ባጋጠመው ችግር አደጋው ስለመፈጠሩ እየተነገረ ነው

ደቡብ ኮሪያ በትናንትናው ዕለት ካጋጠማት አስቸጋሪ የአውሮፕላን አደጋ በኋላ በቦይንግ አውሮፕላኖች ላይ ፍተሻ እንዲደረግ አዛለች፡፡

የሀገሪቱ የመሰረተ ልማት እና የትራንስፖርት ሚኒስቴር በአነስተኛ አየር መንገዶች በስፋት ጥቅም ላይ በሚውለው የቦይንግ 737-800 አውሮፕላኖች ላይ ልዩ ምርመራ እንደሚያደርግ አስታውቋል፡፡

ይህ የተባለው ቦይንግ 737-800 አውሮፕላን ከባንኮክ 18ነ ሰዎችን አሳፍሮ ከሴኡል በስተደቡብ ምዕራብ 290 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው ሙአን ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ለማረፍ ሲሞክር ከግድግዳ ጋር ተጋጭቶ አደጋ መፈጠሩን ተከትሎ ነው፡፡

ቀደም ሲል የደቡብ ኮሪያ ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት ቾይ ሳንግ-ሞክ የአውሮፕላን አደጋ ተደጋጋሚነትን ለመከላከል በሀገሪቱ አጠቃላይ የአየር መንገድ ሥርዓት ላይ የአደጋ ጊዜ ደህንነት ፍተሻ እንዲደረግ ትዕዛዝ ሰጥተው ነበር፡፡

የ179 ሰዎችን ህይወት የቀጠፈው አደጋ መንስኤ በአሁኑ ወቅት በምርመራ ላይ ሲሆን፤ የመጀመሪያ ግኝቶች በማረፊያ ቁሶች ብልሽት አደጋው ስለመፈጠሩ አመላክተዋል፡፡

በዛሬው እለት በጀጁ ኤር የሚተዳደረው ሌላ ቦይንግ 737-800 በተመሳሳይ በማረፊያ መሣሪያው ላይ ባጋጠመው ችግር በደቡብ ኮሪያ ወደሚገኝ አውሮፕላን ማረፊያ መመለሱን የሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙኃን ዘግበዋል ።

ቦይንግ 737-800 አውሮፕላኖች በአብዛኛው የሚንቀሳቀሱት በአነስተኛ በጀት በሚሰሩ የሀገር ውስጥ አየር መንገዶች ነው።

የትናንቱን አደጋ ያስተናገደው ጀጁ ኤር በአሁኑ ጊዜ 39 አውሮፕላኖች ሲኖሩት፤ 62ቱ ደግሞ በቲዌይ ኤር፣ ጂን ኤር፣ ኢስተር ጄት፣ ኤር ኢንቼዮን እና ኮሪያ ኤር በተባሉ አየር መንገዶች ውስጥ ይገኛሉ።

ከአደጋው በኋላም በጀጁ አየር መንገድ ለመጓዝ ትኬት ቆርጠው የነበሩ ደንበኞች በብዛት ጉዟቸውን እየሰረዙ ሲሆን፤ እስካሁን 33 ሺህ የሀገር ውስጥ 34 ሺህ ዓለም አቀፍ በረራዎች በተጓዦች ተሰርዘዋል፡፡

ዮንሀፕ የተባለው የሀገሪቱ ሚዲያ በአሁኑ ወቅት በመላው ደቡብ ኮሪያ ጉዟቸውን ከሚሰርዙ ተጓዦች ባለፈ የአውሮፕላን ትኬት የሚገዙ ሰዎች ቁጥርም በከፍተኛ መጠን መቀነሱን ዘግቧል፡፡

ስፖርት

ከ2024 የማራቶን ድንቅ ብቃቶች መካከል

ብርሃን ፈይሳ

ዛሬ በሚጠናቀቀው የፈረንጆቹ 2024 ከተካሄዱ ዓለም አቀፍ የአትሌቲክስ ውድድሮች መካከል በፓሪስ አስተናጋጅነት የተካሄደው ኦሊምፒክ በቀዳሚነት ይታወሳል። ኦሊምፒክ በበርካታ ስፖርቶች ውድድር የሚካሄድበትና ተወዳዳሪዎችም በድንቅ ብቃት ለመፎካከር ራሳቸውን የሚያዘጋጁበት መሆኑ ትልቅ ትኩረት ይሰጠዋል። በመድረኩ ብቻም ሳይሆን በዓመቱ ከታዩ ኮከብ አትሌቶች መካከል አንዱ ደግሞ ኢትዮጵያዊው የማራቶን አትሌት ታምራት ቶላ ነው።

ከስፖርታዊ ውድድሮች በፈታኝነታቸው ቀዳሚ በሚል በሚቀመጠው ማራቶን ታምራት ቶላ የኦሊምፒክ ወርቅ ሜዳሊያ ሲያጠልቅ በኢትዮጵያ የኦሊምፒክ ታሪክ አምስተኛው አትሌት ለመሆን ችሏል። ይህ የሆነው ደግሞ የመድረኩን ክብረወሰን 2:06:26 በሆነ ሰዓት በማሻሻል ጭምር መሆኑ ክብሩን እጥፍ ያደርገዋል። ይህንን የአትሌቱን ድንቅ ብቃት የተመለከተው የዓለም አትሌቲክስም ዓመቱን በተለያዩ ርቀቶች ከፋፍሎ ሲያስታውስ በማራቶን ለታምራት ተሳትፎና ብቃት ሰፊ ሽፋን ሰጥቷል። የ33 ዓመቱን ወጣት ድል ልዩ የሚያደርገው በቡድኑ በተጠባባቂነት ተይዞ ወደ ፈረንሳይ ካቀና በኋላ በአትሌት ሲሳይ ለማ ጉዳት ተተክቶ በመሮጥ ማሸነፉ ነው።

ታምራት ወደ ጎዳና ላይ ሩጫዎች ፊቱን ከማዞሩ አስቀድሞ በ10ሺ ሜትር ሀገሩን ወክሎ በበርካታ ውድድሮች ውጤታማ ነበር። እአአ በ2016ቱ የሪዮ ኦሊምፒክ በ10ሺ ሜትር የነሐስ ሜዳሊያ ማግኘቱ የሚታወስ ነው። በፓሪስ ደግሞ ሁለተኛውን የኦሊምፒክ ሜዳሊያ ሊያሳካ ችሏል። በወቅቱ የነበረውን ሁኔታም ከዓለም አትሌቲክስ ድረገጽ ጋር ቆይታ ባደረገበት

አትሌት ታምራት ቶላ በፓሪስ 2024 ኦሲምፒክ ማራቶንን ያሸነፈበት አጋጣሚ የውድድር ዓመቱ ትልቅ ክስተት ነበር፤

ወቅት አስታውሷል። ኮረብታዎች በሚበዙበትና ሞቃት በነበረው የአየር ሁኔታ እንዴት ክብረወሰን ሊያስመዘግብ እንደቻለ የተጠየቀው ታምራት «በፓሪስ እጅግ ከባድ ውድድር ቢሆንም በአእምሮዬ መሸነፍ እንደሌለብኝ ሳስብ ነበር። ምክንያቱም ሀገሬ በመም ውድድሮች አንድም የወርቅ ሜዳሊያ ማሳካት አልቻለችም። ማራቶን ደግሞ የመጨረሻው እድላችን በመሆኑ ያለኝን ሁሉ ለማውጣት ጥረት አደረግኩ» ሲል መልሷል።

በውድድሩ ከ27ኛ እስከ 30ኛው ኪሎ ሜትር ያለው ርቀት ዳገታማ መሆኑ ፈታኝ ቢሆንበትም ታምራት ግን ሰዓቱን እያሰበ በመሮጥ ክብረወሰኑን ማሻሻሉ እንዳኮራውም ተናግሯል። «በአትሌቲክስ ፈታኝ ሁኔታዎች የስፖርቱ አካል ናቸው፤ ስለሆነም ሁሌም ለሀገራችን ውጤታማነት እንጥራለን» ሲልም የብርታቱን ምክንያት ጠቁሟል። እአአ በ2022 በዩጂን ዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ላይ ታምራት የወርቅ ሜዳሊያ በማራቶን ለሀገሩ ማስመዝገቡ የሚታወስ ነው። ቻምፒዮናውን ከኦሊምፒኩ ጋር ሲያነጻጽረውም በርካታ የማራቶን ስኬታማ አትሌቶች የተሳተፉበት መሆኑ ከባድ እንደሚያደርገው ተናግሯል።

«በሪዮ ኦሊምፒክ 10ሺ ሜትር ነሐስ ካስመዘገብኩ በኋላ በቀጣዩ ዓመት የለንደን ዓለም ቻምፒዮና በማራቶን ተሳትፌ የብር ሜዳሊያ ነበር ያገኘሁት። ዩጂን ላይ ደግሞ ወርቅ በማጥለቅ በማራቶን ችሎታዬን ማስመስከር ችያለሁ። በዚህም እጅግ ደስተኛ ነበርኩ፤ ምክንያቱ ደግሞ ከረጅም ጊዜ ጉዳት በኋላ ነው ለሀገሬ አሸናፊ የሆንኩት። በ2023 በሆድ ህመም ምክንያት ማሳካት ባልችልም በፓሪስ ኦሊምፒክ ግን የበለጠውን ድንቅ ስኬት አግኝቻለሁ» የፓሪስ ኦሊምፒክ ከመካሄዱ አስቀድሞ ከቡድኑ አባላት (ሲሳይ ለማ፣ ደረሰ ገለታ እና ቀነኒሳ በቀለ) ጋር ለሶስት ወራት ሲለማመድ የቆየው ታምራት በኦሊምፒኩ ባይሳተፍ ኖሮ ዝግጅቱ ለኒውዮርክ ማራቶን ይሆን እንደነበረም ያስታውሳል።

በተጠባባቂነት ተይዞ ውድድሩ ሁለት ሳምንታት ሲቀሩት ተወዳዳሪ እንደሚሆን ሲነገረውም «ደስተኛ ነበርኩ፤ ነገር ግን ለሲሳይ ሀገሩን የሚወክልበት ውድድር በመሆኑ ስሜቱ ቀላል ባይሆንም ተጎድቶ ከመሮጥ እኔ እንድሳተፍ ነበር የነገረኝ። ወደ ውድድሩ ስጓዝም አስብ የነበረው ኬንያዊውን ኢሉድ ኪፕቾጌ እና ሌሎች ጠንካራ አትሌቶችን እንዴት መርታት እንደምችል ነበር። ጠንካራ ልምምድ ማድረጌ እንዲሁም በመጨረሻዎቹ ርቀቶች ወደፊት መውጣቴ ግን ማሸነፍ እንደምችል አረጋገጠልኝ። አንጋፋው አትሌት ገዛኸኝ አበራ ማራቶንን ካሸነፈ በኋላ ላለፉት 24 ዓመታት ኢትዮጵያ በኦሊምፒክ ማራቶን ወርቅ አላስመዘገበችም። በመሆኑም ከረጅም ጊዜ በኋላ ተሳክቶልኝ ከአበበ ቢቂላ፣ ማሞ ወልዴ እና ገዛኸኝ አበራ ጋር ለመጠራት በመብቃቴ ደስተኛ ነኝ። በኦሊምፒኩ ብቸኛውን የወርቅ ሜዳሊያ ለሀገሬ በማስመዝገብ ለሕዝቡ ደስታ ምክንያትም ሆኛለሁ» ሲልም ሁኔታውን አብራርቷል።

ሕብረት ባንክ Hibret Bank

ማስታወቂያ

ስሸቶ ፀደቀ ዓለማየሁ ደበላ በአዋጅ ቁጥር 97/90 እንደተሻሻለ መሰረት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ፤

አቶ ፀደቀ ዓለማየሁ ደበላ ከሕብረት ባንክ አ.ማ አራዳ ሻሸመኔ ቅርንጫፍ የተበደሩትን ብድር ወቅቱን ጠብቀው ባለመከፈልዎ ምክንያት ያዘጋጀነውን የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ በአድራሻዎ ለማድረስ ጥረት ያደረግን ቢሆንም ልናገኝዎ አልቻልንም፡፡ ስለሆነም ይህ ማስጠንቀቂያ በዚህ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሠላሳ ቀናት ውስጥ የብድሩ ቀሪ እዳ በጠቅላላው የማይከፈል ከሆነ ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 97/90 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ለብድሩ በዋስትና የተያዘውን ንብረት በሐራጅ ሸጠን ገንዘቡን ለብድሩ ከፍያ የምናውለው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

ሕብረት ባንክ አ.ማ

ሕብረት ባንክ Hibret Bank

ማስታወቂያ

ስሸቶ ሃውልቱ አብዩ እጅጉ እና ስወ/ሮ አስቴር ተፈራ አድማሱ በአዋጅ ቁጥር 97/90 እንደተሻሻለ መሰረት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ፤

አቶ ሃውልቱ አብዩ እጅጉ እና ባለቤትዎ ከሕብረት ባንክ አ.ማ ደባርቅ ቅርንጫፍ የተበደራችሁትን ብድር ወቅቱን ጠብቃችሁ ባለመክፈላችሁ ምክንያት ያዘጋጀነውን የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ለእርስዎ እና ለባለቤትዎ በአድራሻችሁ ለማድረስ ጥረት ብናደርግም ልናገኛችሁ አልቻልንም፡፡
ስለሆነም ይህ ማስጠንቀቂያ በዚህ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሠላሳ ቀናት ውስጥ የብድሩን ቀሪ እዳ በጠቅላላው የማትከፍሉ ከሆነ ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 97/90 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ለብድሩ በዋስትና የተያዘውን ንብረት በሐራጅ ሸጠን ገንዘቡን ለብድሩ ከፍያ የምናውለው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

ሕብረት ባንክ አ.ማ

ሕብረት ባንክ Hibret Bank

ማስታወቂያ

ስቄስ ሳስም ብርሃን አያል እና ስባስቤትዎ ወ/ሮ ያልጋ እንግዳ ጌቴ በአዋጅ ቁጥር 97/90 እንደተሻሻለ መሰረት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ፤

ቄስ ላለም ብርሃን አያል እና ባለቤትዎ ከሕብረት ባንክ አ.ማ ቁጭ ቅርንጫፍ የተበደራችሁትን ብድር ወቅቱን ጠብቃችሁ ባለመክፈላችሁ ምክንያት ያዘጋጀነውን የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ለእርስዎና ለባለቤትዎ በአድራሻችሁ ለማድረስ ጥረት ብናደርግም ልናገኛችሁ አልቻልንም፡፡
ስለሆነም ይህ ማስጠንቀቂያ በዚህ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሠላሳ ቀናት ውስጥ የብድሩን ቀሪ እዳ በጠቅላላው የማትከፍሉ ከሆነ ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 97/90 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ለብድሩ በዋስትና የተያዘውን ንብረት በሐራጅ ሸጠን ገንዘቡን ለብድሩ ከፍያ የምናውለው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

ሕብረት ባንክ አ.ማ

አማራ ክልል

ንብረትነቱ የይመር መሐመድ የሆነ ባጃጅ ተሽከርካሪ የሰሌዳ ኮድ 01-32897 አማ ሰሌዳ የጠፋ መሆኑን ባለንብረቱ በ27/3/2017 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡
ሰሌዳው ወድቆ ተሰርቆ ወይም በሌላ ግለሰብ እጅ ላይ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ሪፖርት እንዲያደርግ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

በደ/ወሎ ዞን ትራንስፖርት ጽ/ቤት

ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም Tizita Damiro Afawarq የሰሌዳ ቁጥር OR-01-31397 የሊብሬ ቁጥር 000486807
ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት ሰሌዳ ወድቆ ጠፋብኝ ብለው በ11/04/2017 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡
በዚሁ መሰረት የመኪና ሰሌዳ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይገዜዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍርድቤትማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ካላቀረቡ ለአመልካች ሰሌዳ በምትክ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

የአዳማ ከተማ ትራንስፖርት ባለስልጣን

አፋር ክልል

ንብረትነቱ የአቶ ሲሳይ መዝገቡ መኩብብ የሆነ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-01622 አፋ የሆነ አውቶቢስ ተሽከርካሪ የሞተር ቁጥር 2082722 የሻንሲ ቁጥር RZH113-0034867 የኋላ ሰሌዳ ወድቆ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ባቀረቡልን ማስረጃ መሰረት በእዳ ወይም በሌላ ምክንያት ይገዜዋለሁ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያሳወቅን በተባለው ጊዜ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሰሌዳ የሚሰጣቸው መሆኑን እገልጻለን፡፡

የአፋር መንገድ ልማት ትራንስፖርት ቢሮ

አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ፀጋዬ መኮንን በቀለ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A63029 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር JT1POLN6504023106 ሞዴል 1N65L-MPW የሞተር ቁጥር 21-1652605 የሊብሬ ቁጥር 049439
ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ14/4/2017 ዓ.ም አመልክተዋል።
ሰሌዳው ወድቆ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቂርቆስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

በከሳሾች/አመልካቾች አቶ ቃል ግሩም ምክሩ አቶ ዳዊት ሃብታሙ አበራ እና በተከሳሽ/በተጠሪ አቶ ብሩክ ቦጋለ ተሰማ መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድ ምድብ 1ኛ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ተጠሪ በ28/04/2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ስላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍርድ ቤቱ አዟል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት
ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት

የባለንብረት ስም ሰለሞን ገ/ሕይወት ተሰማ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A41015 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JALK6A135G7102223 ሞዴል FSR6MF የሞተር ቁጥር 6HH1-487158 የሊብሬ ቁጥር 495639/587183/112180/178732/371889
ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ14/4/2017 ዓ.ም አመልክተዋል።
ሠሌዳው ወድቆ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የጦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

የባለንብረት ስም ዛይ ትራንስፖርት አገልግሎት ኃላ/የተ/የግ/ማ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-44661 የተሽከርካሪው አይነት አውቶቡስ (ከ11 የበለጠ መቀመጫ) የሻንሲ ቁጥር LKLS1CSB57A123681 ሞዴል KLQ6728 የሞተር ቁጥር 69456663 የሊብሬ ቁጥር 420266
ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ29/11/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳው ወድቆ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

በአመልካች አቶ አማኑኤል ተስፋዬ ምንዳ እና በተጠሪ ወ/ሮ ራሔል ብርሐኑ ገ/ማሪያም መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክስ ጉዳይ ተጠሪ ወ/ሮ ራሔል ብርሃኑ ገ/ማሪያም በ05/05/2017 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ኮ/ቀ ምድብ 3ኛ ቤተሰብ ችሎት እንዲቀርቡ እንገልፃለን፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት

በከሳሽ/ሾች/በአመልካች/ቾች/በፍ/ባለመብት/ቶች ስኬት ባንክ አ/ማ እና በተከሳሽ/በተጠሪ/በፍ/ባለእዳ/ዎች እነ ትዕግስቴ ፣ ነጃ እና ጓደኞቻቸው መካከል ስላለው ክስ ጉዳይ በተከሳሽ/ሾች/በተጠሪ/ዎች/ በፍ/ባለእዳ/ዎች 1. ሰይፉ ተማሞ 2. አበባው አየለ 3. ዮሴፍ ብርሐኔ በ25/04/2017 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ጠዋት 4፡00 ሰዓት ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ኮ/ቀ ምድብ 2ኛ ል/ል ችሎት እንዲቀርቡ እንገልፃለን፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት